*"በዚህ ምድር ላይ በስኬታማነት የሚኖሩ ሰዎች ጠዋት ተነስተው የሚጠባበቁትን አመቺ ሁኔታ ሲፈልጉ ካላገኙት ያንን ሁኔታ ወደ መኖር ለማምጣት ተግተው የሚሰሩ ሰዎች ናቸው" - George Bernand Shaw*

አንድ አንድ ጊዜ የጠበካቸውን መልካም ነገሮች አታገኝም:: አንዳንዴ ደግሞ ያልጠበካቸው ተራራዎች በፊትህ ይደነቀሩብሃል:: ይህ ሲሆን ምርጫህ ሁለት ነው - አንደኛው ምርጫ፣ አእምሮህን በአሉታዊ ሃሳብ በመሙላት "ለምን እንዲህ ሆነ?" የሚለውንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በአእምሮህ በማጉላላት መኖር ነው:: ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ፣ "ሁኔታውን እንዴት ልለውጠው?" በሚል የፈጠራ ጥያቄ በመሞላት አእምሮን ለመፍትሄ ማሰራት ነው:: የእኔ ምርጫ ሁለተኛው ነው፤ የአንተስ?

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው፣ ነገሮችን ወደ መኖር የማምጣት ቁልፎች:-

1. አመለካከትህንና አደራረግህን ለውጥ
2. መቆጣጠር የምትችለው ላይ አተኩር
3. ስለ ሁኔታህ አትነጫነጭ

*"ጨለማውን መቶ ጊዜ ከምትረግመው ይልቅ አንዲትን ሻማ ማብራት ይመረጣል"*





# 13

# ኤቨረስት ሆይ፣ አሸንፍሃለሁ

## ራስን የማሻሻል ቁልፍ



አንድ ሰው ተሸነፈ የሚባለው መቼ ነው? በቃኝ ብሎ ሲያቆም ነው:: ብዙ ሰዎች ለረጅም ጊዜ የለፉለት ነገር ድል ሲቃረብ ተስፋ በመቁረጥ ጥለውት ይሄዳሉ:: በነበራቸው ጥረት ውስጥ ያዳበሩትን ጥንካሬ አያስተውሉትም:: ብዙ ሞክሮ አለመሳካት ያለማቆም እንጂ የማቆም ምክንያት ሊሆን አይገባውም፣ ምክንያቱም በተሞከረው ሙከራ የመጣው ጥንካሬ፣ የባህሪይ ጽናትና የልምምድ ብስለት ከመሞከራችን በፊት የነበረንን የማሸነፍ ብቃት በብዙ እጥፍ ስለሚጨምረው ነው:: ሞክረን ስንሸነፍ፣ ራሳችንን አሻሽለን እንደገና ብንሞክረው እንደምናሸንፈው ማረጋገጫችን እንደሆነ ማወቅ አንዱ የስኬት ቁልፍ ነው::

ሰር ኤድመንድ ሂለሪ (Sir Edmund Hillary) ለመጀመሪያ ጊዜ የኤቨረስትን ተራራ ጫፍ የረገጠ ሰው ነው:: ይህንን ተራራ በድል ተወጥቶት ጫፍ ከመድረሱ በፊት በነበረው የቀድሞ ሙከራው ቡድኑ ተራራውን መውጣት አቅቶት አንድ ሰው ሞቶባቸው ተመልሰው ነበር:: ከዚያ አሳዛኝ ሙከራቸው ሲመለሱ በለንደን በነበረው ሪሰብሸን ግብዣ ላይ ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ነበር:: ቆሞ ንግግር ከሚያደርግበት መድረክ ጀርባ የኤቨረስት ተራራ ምስል በትልቁ ተቀምጧል:: በንግግሩ ወቅት ወደዚህ



Scanned with CamScanner

የተራራ ስእል ዘወር በማለት እንዲህ አለ፣ "ኤቨረስት ሆይ፣ አሁን አሸንፈኸናል:: ነገር ግን ጠብቀኝ እመለስና አሸንፍሃለሁ ምክንያቱም አንተ ያው ነህ፣ እኔ ግን አድጌና በርትቼ እመለሳለሁ":: እነዚህ ቃላት ከተናገረ በኋላ ነበር የሚያስፈልገውን ዝግጅት አድርጎ ቀድሞ ያሸነፈውን ተራራ ሄዶ ያሸነፈው::

*"ታላቁ ክብራችን ያለው ባለመውደቅ ውስጥ አይደለም፣ በወደቅን ጊዜ ሁሉ ተነስተን በመቀጠላችን ውስጥ ነው እንጂ" - Ralph Waldo Emerson*

መራመድ እስካለ ድረስ መውደቅ አለ፣ መነገድ እስካለ ድረስ መክሰር አለ፣ መውደድ እስካለ ድረስ መጎዳት አለ፣ መማር እስካለ ድረስ ፈተና መውደቅ አለ ... ይህ የማይለወጥ የሕይወት ህግ ነው:: "ምን ይበላሽ ይሆን?" በሚለው ፍርሃት ታስሮ መንቀሳቀስ አለመቻል በሕይወት እያሉ መሞት ነው:: ብዙ ሰዎች ሕይወቱ ያልፍ ይሆናል ብለው ከመፍራታቸው የተነሳ ሕይወትን ሳይጀምሯት ያልፋሉ:: ሕይወት ግን አዳዲስ ነገሮች የሚሞከሩባት፣ ሲሳካ የምንደሰትባት፣ ሳይሳካ ደግሞ ራሳችንን ከወደቅንበት አንስተንና አቧራችንን አራግፈን እንደገና የምንቀጥልባት ጎዳና ነች::

ሕይወት ማለት በዚህ ምድር ላይ "መከሰትና" ምንም ነገር እንዳይደርስብን ራሳችንን መጠበቅ አይደለም:: "ለአደጋ" ሊያጋልጡን የሚችሉትንና ማንነታችንን የሚፈቱትን ነገሮች ከመሞከር ውጪ ሕይወት ባዶ ነች:: ለዚህ እውነታ ልባችንን በመክፈት አዳዲስ "ተራራዎችን" በመውጣት፣ ሰው ያልሞከረውን በመሞከርና በማንነታችን ውስጥ የታመቀውን ድብቅ ብቃት የሚወጣበትን እድል ልንሰጠው የግድ ነው:: ጥቂት እውነታዎች:-

## የማይወድቅ ሰው የማይንቀሳቀስ ሰው እንደሆነ አስታውስ

በፍጹም ላለመውደቅ ከፈለግህ ቀላሉ መንገድ በፍጹም አለመራመድ ነው:: አለቀ! አለመራመድ፣ የውድቀት ሁሉ ውድቀት! ቁጭ ብሎ መውደቅ፣ አካል ተደላድሎ ልብና





ወኔ ግን ወድቆ! የወደቀ ሰው ማን ነው? አደጋ ፍራቻ የተከተተ ሰውአይደለምን? ሳይፈተን ፈተናውን የወደቀ ማንነው? ፈተና መውደቅን ፈርቶ አለመማርን የመረጠና አለማወቅ የጣለው ሰው አይደለምን? መውደቅ? የትኛው አይነት መውደቅ? ሞክሮ መውደቅ ወይስ ሳይሞክሩ ውዳቂ መሆን? ሞክሮ መውደቅና ከውድቀቱ ትምህርትን አግኝቶ ለማሸነፍ መውጣት ወይስ ለመሞከር ሳይነሱ በዚያው ወድቆ መቅረት? ውድቀት ለሚለው ቃል አዲስ ትርጓሜ የምንሰጥበት ዘመን ነው!!! ውብ የሆነን ነገር ወደመኖር ለማምጣት ሞክረንና ጥረን የገጠመንን የሁኔታዎች መቃወስውድቀትና ስህተት ብለን የምንጠራው ተስፋ ቆርጠን በዚያው ከቀረን ነው:: በተቃራኒ ግን፣ እንደገና ተነስተን የምንሞክር ከሆነ፣ ስህተቱን ትምህርት በሚል ትርጉም መለወጥ አለብን::

*"ያልተለመደውን ነገር የማድረግን አደገኛነት ለመጋፈጥ ፈቃደኛ ካልሆንክ ለተለመደው ነገር ሰከነህ ትኖራለህ" – Jim Rohn*

የተለመደው ነገር ከተመቸህ፣ መልካም ነው - ይመችህ! አሁን ካለህበት ሁኔታ አልፈህ ለተሻለ ነገር የመስራቱ ጥቅም ካልታየህና ባለህበት ከተደላደልክ፣ ግሩም ነው:: ይህ አመለካከት ግን የስኬታማ ሰዎች አመለካከት እንዳልሆነ ሳላስታውስህ አላልፍም::

በአዲስ እይታ ወደ አዲስ ደረጃ ለመዝለቅ መንቀሳቀስ አደገኛነት አለው:: የዚህ ምርጫ አደገኛነቱ፣ ወደማታውቀው ቀጠና የመዝለቅና አዳዲስ ችግሮችን የመጋፈጥ አደገኛነት ነው:: ውጤቱ ግን አስገራሚና አርኪ ነው:: በአንጻሩ፣ ባለህበት ለመቆየት የምታደርገውም ምርጫ የራሱ የሆነ አደገኛነት አለው:: ባለህበት የመርጋትህ ትልቁ አደገኛነት ወደ ኋላ የመቅረት ጉዳይ ነው:: የአለም እውነታ በፍጥነት በሚለወጥበት በዚህ ዘመን ባሉበት መቆም የሚባል ነገር እንደሌለ እወቅ:: ወይ ወደ ፊት ትሄዳለህ ወይም ደግሞ ወደ ኋላ ትቀራለህ፣ ወይ ታድጋለህ ወይም ደግሞ ታንሳለህ:: ምርጫው የአንተ ነው:: ወደ ፊት በመንቀሳቀስ ከሚገጥምህ አደጋ ይልቅ ባለህበት የመቆየቱ አደጋ እጅግ የከፋ ነው::



Scanned with CamScanner

## ውስጥህን በይቻሳል ሙሳው

ያልተሞከረንና ከባድ የተባለውን ሕልምህን ያለማድረግ ዝንባሌ ቀድሞውኑ ካለህ፣ “አልችልም” የሚለውን አባባልህን “ላለመቻል ወስኛለሁ” በሚል ብትቀይረው ይሻላል:: ምክንያቱም አለመቻል የውሳኔ ጉዳይ ነው:: ውስጥን በይቻላል መሙላት ማለት የውሸትና የማይሞላ ቅዠት ውስጥ መኖር ማለት አይደለም:: እውነተኛን ራእይ የያዘ ሰውና ለስኬት ራሱን በማዘጋጀት ላይ ያለ ሰው “የቀን ሕልምን” ቁጭ ባለበት ከሚያልም ሰው ይለያል:: “በቀን ሕልም” ምኞት የሚወሰድ ሃሳብ ያለው ሰውና በራእይ የሚቃጠል ልቦና የሞላበት ሰው ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው:: ቁጭ ብለህ ምኞትህን እያሰብክ “ይቻላል” ብትል የትም አትደርስም:: በአይነ-ህሊናህ ወዳየኸው አቅጣጫ ለመገስገስ አስፈላጊውን እርምጃ በመራመድ፣ “እችላለሁ” ማለትህ ግን ማንነትህን የሚፈታ አስፈላጊ ዝንባሌ እንደሆነ አትዘንጋ:: እውነተኛ የ“እችላለሁ” አመለካከት ምልክቱ በተግባር በመደገፉ ጉዳይ ነው::

*“አብዛኛውን ጊዜ ያልተቻለው ነገር ከዚህ በፊት ያልተሞከረው ነገር ነው” - Jim Goodwin*

“እችላለሁም ካልክ፣ አልችልምም ካልክ ትክክል ነህ” የሚለውን አባባል ምናልባት ከዚህ በፊት ሰምተኸው ይሆናል:: መቻልም ሆነ አለመቻል የአመለካከትና የዝንባሌ ጉዳዮች ናቸው:: “እችላለሁ” የሚለው እምነት፣ ስሜትህን፣ ፈቃድህንና ፍላጎትህን በማስተባበር አእምሮህ ለመፍትሄ ከማሰብ ይልቅ ሌላ ምርጫ እንዳይኖረው የማድረግ ተጽእኖ ያሳድርበታል::

ማታ “እችላለሁ” በሚል አዎንታዊ አሳብ ስትተኛ ማንነትህ መፍትሄን አሰላስሎና አልሞ ያድራል:: ይህ ብዙ ስኬታማ ሰዎች የተጠቀሙበት ቁልፍ ነው:: አንተም ብትጠቀምበት አዲስ ደጅን ይከፍትልሃል:: በተቃራኒው፣ “አልችልም” የሚለው ንግግርህና





አመለካከትህ ማንነትህ ለአዲስ ነገር ከመንቀሳቀስ ይልቅ እንዲለግም ያደርገዋል:: “ስኬታማ ሰዎች በይቻላል የተሞሉበት ምክንያት ሁሉም ነገር ስለሞላላቸው ነው” ብለህ ካሰብክ ተሳስተሃል:: በተቃራኒው፣ እነዚህ ሰዎች ቀድሞውኑ በይቻላል ተሞልተው ነው አሁን ያሉበት ደረጃ የደረሱት::

## ራስህን ካስማቋረጥ አሻሽል

ትናንት ሞክረህ ያቃተህን ነገር በትናንትና እውቀትህና ያኔ በተጠቀምክበት ዘይቤህ አንደገና አትቅረበው:: ራስህን ካለማቋረጥ አሻሽል:: ተማር፣ ልምድን ቅሰም፣ ከአንተ በፊት በአንተ ሁኔታ ያለፉትን ጠይቅ፣ ራስህን በመረጃ አጠናክር፣ ደካማ ጎንህን አበርታ … ከዚያም እንደገና ተራራህን ለመውጣት ተነሳ፣ ትችለዋለህ! ይህንን ለማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ትችላለህ:: “ባለፈው ስሞክር የማላውቀው ነገር ምንድን ነበር? አሁን ባውቀው መፍትሄ የሚሰጠኝ የእውቀት አይነትስ የትኛው ነው?” “ባለፈው ስሞክር የነበረኝ ደካማ ጎን ምንድን ነበር?” “አሁን ምን ያህል ራሴን አዘጋጅቻለሁ?” “ሁኔታውን በምን መልኩ ልቅረበው?” እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አሮጌውን ችግርህን በአዲስ ጉልበትና አመጣጥ እንደገና በመግጠም ልታሸንፈው ትችላለህ::

*“ዘወትር ታደርገው የነበረውን ነገር በማድረግ ከቀጠልክ፣ ዘወትር ታገኘው የነበረውን ያንን ውጤት ታገኛለህ” – Tony Robbins*

ለምሳሌ፣ የዛሬ አንድ መቶ አመት እንጠቀምበት የነበረውን የግብርና ዘይቤ አሁንም ስንጠቀም የዛሬ አንድ መቶ አመት ስናገኘው የነበረውን ፍሬ እናገኛለን:: ሁኔታው ግን እዚህ ላይ ብቻ አያቆምም:: የዛሬ አንድ መቶ አመት ያስቸግረን የነበረው ችግር አሁንም በዚያው ዘይቤ ስንታገል እንኖራለን:: ችግር በራሱ ምንም “ችግር” የለበትም:: ችግር በእኛ ላይ “ችግርን” የሚያመጣው ለችግሩ መፍትሄ የሚሰጥን ማንነትና ብቃት ሳናዳብር



Scanned with CamScanner

ስንጠብቀው ነው:: ዛሬ ማንሳት ያቃተህን ክብደት ለማንሳት ጡንቻህን አሻሽለህ መመለስ የግድ ነው::

ክብደቱ ያው ነው፣ አንተ ግን ተለውጠሃል:: ዛሬ ማለፍ ያቃተህን ፈተና ለማለፍ እውቀትህን አሻሽለህ መመለስ አስፈላጊ ነው:: ፈተናው ያው ነው፣ አንተ ግን ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ አውቀህ ታጥቀሃል:: ራስን ማሻሻል ሌላ አማራጭ የሌለው ብቸኛ ምርጫህ ነው::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ራስን የማሻሻል እውነታዎች:-

1. የማይወድቅ ሰው የማይንቀሳቀስ ሰው እንደሆነ አስታውስ
2. ውስጥህን በይቻላል ሙላው
3. ራስህን ካለማቋረጥ አሻሽል

*"ለአደጋ" ሊያጋልጡን የሚችሉትንና ማንነታችንን የሚፈቱትን ነገሮች ከመሞከር ውጪ ሕይወት ባዶ ነች::*





# 14

# የውሻዬና የመኪናው ነገር

## የሚፈልጉትን የማወቅ ቁልፍ



ሰው ቢደርስበትና በእጁ ቢጨብጠው ለምንም የማይጠቅመውን ነገር በመከተል ጊዜውን የሚያባክነው ለምንድን ነው? አሁን በብርቱ የምትከታተለውን፣ ብዙ ጊዜህን የምታጠፋበትን፣ ገንዘብህን ያባከንክበትን ነገር በእጅህ ብታስገባው፣ በህይወትህ ካለህ ዋነኛ ዓላማ ጋር አብሮ ካልሄደና ወደትምሄድበት የሕይወት አቅጣጫ አንድ እርምጃ ካላራመደህ ጊዜህን በከንቱ እያባከንክ ነው:: ድካምና ነፋስን እንደመከተል ይሆንብሃል - የማያዛልቅን ነገር ማባረር! የምትከተለው ነገር በምትሄድበት የሕይወት ዓላማ አቅጣጫ መሆኑን ማወቅ የአዋቂነት ሁሉ አዋቂነት ነው:: መመለስ ያለበት ጥያቄ፣ "የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው?" የሚለው ነው::

አንድ ሰው ለወዳጁ እንዲህ ብሎ አጫወተው:: "የውሻዬና የመኪናው ነገር በጣም ነው ያደከመኝ:: በሰፈራችን ያለፈው መኪና ሁሉ አንድም አይቀረውም፣ በብርቱ እየተከታተለ ይጮሃል:: ያየውን መኪና ሁሉ ለተወሰነ ርቀት ካሳደደው በኋላ ተመልሶ ይመጣል:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና ሌላ መኪና ሲመጣ ጠብቆ ያንኑ ነገር ይደግማል:: ስለእርሱ እኔ ደከመኝ":: ወዳጁ ይህንን ከሰማ በኋላ አንድ ጥያቄ ጠየቀው፣ "ለመሆኑ፣ ውሻህ መኪናን አባርሮ የሚደርስበት ይመስልሃል?" ሰውዬውም መልሱ

የሚጣፍጠው ለአንተው ነው:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፣ የምታደርጋቸውን ነገሮች ለታይታ የምታደርግበት ምክንያቱ ለምን ይመስልሃል? ነገሩን ተረጋግተህ አስበው::

አንድን ነገር ስትተገብር የሚያዩህ ሰዎች ሊኖራቸው የሚችለውን ሃሳብ እዚሁ አስበህ ልትደርስበት ትችላለህ:: አብዛኛዎቹ ሰዎች ቀድሞውኑ ዘወር ብለውም አያዩህ:: አንዳንዶቹ፣ ያደንቁህና መንገዳቸውን ይሄዳሉ፣ ሌሎቹ፣ ለታይታ እንዳደረከው ያስቡና መንገዳቸውን ይቀጥላሉ:: ሌሎቹ ደግሞ፣ አንተ ለታይታ ብለህ የምታደርገውን ነገር እንደ ትንሽ ነገር ስለሚቆጥሩት የምታሳየውን "ተራ" ትእይንት አይተው "ምስኪን ብለውህና አዝነውልህ ያልፋሉ:: ወሳኙ ነገር የእነዚህ ሁሉ ሰዎች አሳብ ተሰንዝሮ ካለቀ በኋላ አንተ የምትኖረው ኑሮ ነው:: ከዚህ ሁሉ ያመንከበትንና የፈለግከውን ነገር ምን እንደሆነ ለይተህ አውቀህ ያንን መኖር ይሻልሃል::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው የሚፈልጉትን የማወቅ መመሪያዎች:-

1. አንድን ነገር ስላማረህ ብቻ አትከታተለው
2. አንድን ነገር ሰዎች ሁሉ ስለ ተከተሉት አትከተለው
3. አንድን ነገር ብቃትህን ለማስመስከር ብለህ አትከተለው

> አንድን አስፈላጊ ነገር ለመግዛት ወደገበያ ሄዶ ያየውንና ለአይኑ ያማረውን ሁሉ ገዝቶ የሚመጣን ሰው ምን ትሉታላችሁ?





# 15

# ለትምህርት የሆነ ስህተት

## ስህተትን ለትምህርት የመለወጥ ቁልፍ



የሚሳሳት ሰው ማን ነው? አንድን ነገር የሚሞክር ሰው አይደለምን? የሚደናቀፍና የሚወድቅ ማን ነው? የሚራመድና የሚንቀሳቀስ ሰው አይደለምን? የሚጎዳና የሚቆስል ማን ነው? ለመውደድ ራሱን የሚሰጥ አይደለምን? ካልሞከርን እንዴት እንደርሳለን፣ ከውድቀት ውጪስ እንዴት እንሞክራለን? ምርጫችን ከሁለት አንድ ነው:: አንደኛው ምርጫ፣ ሰው ሁሉ እንደሚያደርገው ችግር የሌለበትን ቀላል ነገር በመምረጥ ሳይንቀሳቀሱ ተዳላድሎ መኖር ነው:: ሁለተኛው ደግሞ፣ ያልተሞከረን ሞክሮና ሲወድቁ ተነስቶ አዲስ ነገር ውስጥ መግባት:: የእኔ ምርጫ ሁለተኛው ነው - የአንቺስ? የአንተስ?

ቶማስ ኤዲሰን (Thomas Edison) ብርሃን ሰጪ አምፖልን ለመፈልሰፍ ባደረገው ሙከራ ቢያንስ አንድ ሺህ ጊዜ ሞክሮ እንዳልተሳካለት ያየ ሰው፣ "ይህን ያህል ሞክረህ አልተሳካም፣ አይበቃህም?" ብሎ እንደጠየቀው ይነገራል:: ለዚህ ጥያቄ የሚያስገርምን መልስ እንደሰጠውም ይነገራል:: "አንድ ሺህ ጊዜ አልተሳካልኝም ብዬ አይደለም የምቆጥረው፣ አንድ ሺህ የሚያክሉ አምፖልን ወደመሆን ማምጣት የማይቻልባቸውን



Scanned with CamScanner

መንገዶች ነው የተማርኩት - ለትምህርት የሆነ ስህተት":: ቶማስ ኤዲሰን እነዚህ ቃላቶች ከተናገረ በኋላ ባደረገው ሙከራ ብዙ የለፋበት ግኝት ላይ ለመድረስ በቃ::

*"በውድቀት የሚታወቁ ሰዎች፣ ተስፋ ቆርጠው ባቆሙበት ሰዓት ምን ያህል ለውጤት ቅርብ እንደነበሩ ያላስተዋሉ ሰዎች ናቸው" - Thomas Edison*

በሕጻንነትህ ቀና ለማለት ሞክረህ በስንተኛው የተሳካልህ ይመስልሃል? ለመዳህና ዳዴ ለማለትስ ያደረከው ሙከራህ ምን ያህል አደከመህ? በእግርህ ለመቆም ስንት ጊዜ ፈጀብህ? ስንት ጊዜ እጆችህ የሙጥኝ ብለው የያዙትን ወንበር ከለቀቁ በኋላ ተመልሰው ይዘውታል፣ ስንቴስ ወደምድር አጎንብሰህ ራስህን አድነሃል? ለመራመድ ባደረከው ሙከራስ ስንት ጊዜ ወድቀሃል? እነዚህ ልምምዶችህን ቆጥረህ "ሁለተኛ ለመራመድ አልሞክርም" አለማለትህን አስተውለህ ታውቃለህ? ዛሬ እንደልብህ የምትንቀሳቀሰው ከስህተትህ ባሻገር አልፈህ ስለመጣህ ነው:: ትወድቃለህ፣ ውዳቂ ግን አይደለህም:: ትሳሳታለህ፣ ስህተተኛ ግን አይደለህም፣ ትሸነፋለህ ተሸናፊ ግን አይደለህም:: ያሳለፍከው የስህተት ልምምድ ሁሉ በአንተነትህ ላይ በሌላ መልኩ ልትማራቸው የማትችላቸውን አስገራሚ ትምህርቶችን ትተውልህ አልፈዋል::

ይህ እይታ ልምምዶችህንና ያሳለፍካቸውን ነገሮች አልለወጣቸውም፣ ለእነዚህ ሁኔታዎች ያለህን ምላሽ ግን በሚገባ ይለውጠዋል:: ይህ አስገራሚ እይታ እያንዳንዱን ከስተት ወደትምህርትና ለእድገትህ ወደመጠቀም ይለውጥልሃል::

ስህተትን ወደ ትምህርት ለመለወጥ የሚያስችሉ እይታዎች:-

## የስህተትን እውነታ ተቀበል

ከወዲሁ ቁረጥ፣ ስህተት በፍጹም አይቀርም:: ስህተት መስራት የለብኝም የሚለው ሃሳብ የቅዠት ሃሳብ ነው:: ስህተትን በፍጹም መስራት የለብኝም ብሎ የሚያስብ ሰው





ከመሆን የማይቀረውን ስህተት ሲሰራ ስህተቱ ሁለት ይሆንበታል፤ በአንዱ ጎኑ የሰራው ስህተት፣ በሌላው ጎኑ ደግሞ ስህተት እንደ እንግዳ ነገር የመቁጠሩና በነገሩ የመረበሹ ስህተት:: ተሸናፊዎች፣ "ለምን ተሳሳትኩ" በማለት በራሳቸው ላይ ይፈርዳሉ:: ተሸናፊዎች አሸነፊዎች ግን ከስህተታቸው ትምህርታቸውን ለቅመው ያልፋሉ:: ተሸናፊዎች ራሳቸውን በጭካኔና "በኮስታራነት" ያዩታል፤ አሸነፊዎች ስህተታቸውን አምነው ይቀበላሉ ሆኖም በራሳቸው "ይስቃሉ"፣ የራሳቸውንም ትከሻ ዳበስ በማድረግ፣ "አይዞኝ" በማለት ወደ ፊት ይዘልቃሉ:: ተሸናፊዎች "ስህተት በፍጹም መከሰት የለበትም" በማለት ያስባሉ፤ አሸናፊዎች ግን እውነታውን በመቀበል አልፈው ለመሄድ የተዘጋጀ ልቦና አላቸው፡

*"በስኬቶቼ ካገኘኋቸው ትምህርቶች ይልቅ ከስህተቶች ያገኘኋቸው ትምህርቶች ይልቃሉ" – Humphry Davi*

አንዳንድ በአስተዳደር ስራ ላይ የተሰማሩ "አለቆች" በስራቸው የተሰማሩ ሰራተኞች ምንም ስህተት እንዳይሰሩ ወጥረው ይይዟቸዋል:: ስህተት የመስራቱን ሁኔታ ለመቀነስ በሚያደርጉት ጥረት አዳዲስ አደራረጎችን ይገታሉ:: ሰራተኞቹ ስራውን እንደራሳቸው በመውሰድ አዳዲስ የፈጠራ መንገዶችን እንዳይሞክሩ ይያዛሉ፣ ምክንያቱም ስህተት ከተሰራ ሊደርስባቸው የሚችለውን ቅጣት ስለሚያስቡ:: በልጅ አስተዳደግ ላይም ይህ ድካም ጎልቶ ይታያል:: ምንም ስህተት እንዳይሰራ ታፍኖ የኖረ ልጅ ሲያድግ የራሱና የህብረተሰብ ጠንቅ ነው::

እድገ የሕብረተሰቡ አካል ሲሆን፣ በሰራው ስህተት ሁሉ ራሱን የሚኮንን ሰው ይሆናል:: ከዚያም አልፎ አንድ ስህተት ሲገኝ ስህተቱ የሚታረምበትን መንገድ ከመፈለግ ይልቅ ስህተቱን የሰራውን ሰው ማውጣጣትና ሰውየውም የሚቀጣበትን መንገድ መፈለግ ይቀናዋል:: ይህ አመለካከት የእድገት ጠንቅ ነው:: እውነት ነው፣ አንድ ነገር ሲሳካልን ከምናገኛቸው ትምህርቶች ይልቅ ስንሳሳት የምናገኛቸው ትምህርቶች እጅግ የላቁ ናቸው::

# 17

## የሚጀመሩ፣ ነገር ግን የማይጨረሱ

### ጀምሮ የመጨረስ ቁልፍ



ያልተጨረሱትን ሃውልቶች እያዩ "መጨረሻው ምን ሊመስል ይችል ነበር?" ማለታቸው አልቀረም:: ሰዎች በተጨረሱት ስራዎቹ አንድን ነገር ጀምሮ የመጨረስን አይታ የመካፈላቸውን ያህል፣ ባልጨረሳቸውም ስራዎቹ ያለመጨረስ ዘር በውስጣቸው መዘራቱ የማይቀር ነው:: እነዚህ ተጀምረው ያልተጨረሱ የማይከል አንጀሎ ስራዎች፣ ወደሙላት ያልደረሱ በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ያሉ፣ የሚጀመሩ፣ ነገር ግን የማይጨረሱ አስገራሚ እምቅ ብቃቶች ምልክት ናቸው!

*"ተጀምሮ እንዳልተፈጸመ ስራ በሰው ማንነትና ባህሪይ ላይ ጥላ የሚያጠላ ነገር የለም" - David George*

ይህንን መጽሐፍ ማንበብህ በጥቂቱም ቢሆን የማንበብ ልማድህን ያሳያል:: ከዚህ በፊት ያነበብካቸውን መጸሕፍ መለስ ብለህ ማግኘት ከቻልክ ተመልከታቸው፣ ያቀለምካቸውና ያሰመርከባቸው ሃሳቦች ያሉት የመጽሐፉ መጀመሪያ ገጾች ላይ ብቻ ከሆነ ምናልባት ያንን መጽሐፍ ማንበብ ጀምረህ አልጨረስከውም::

እስከዛሬ የጀመርካቸውን ፕሮጀክቶች አስባቸው፣ የትኛዎቹን እስከጥግ ወስደሃቸዋል? ገና በሃሳብ የቀሩት ድንቅ እቅዶችህ፣ ገና እንደተጀመሩ የተቀጩት አስገራሚ ጅማሬዎችህ፣ ብዙ ከለፋህና ዋጋ ከከፈልክባቸው በኋላ የተውካቸው ህልሞችህ ... :: ያቋረጥከውን ነገር እንደገና ለመጀመር ጊዜው አልዘገየም:: ጀምረኸው ሳትጨርስ ወደተውከው ነገር እንደገና የመመለሻውና ካቆምክበት የመቀጠያው ትክክለኛው ጊዜ ውሳኔን የምታደርግበት ጊዜ ነው:: ተጀምሮ የቆመ ትምህርት፣ ተጀምሮ የቆመ መጽሐፍ፣ ተጀምሮ የቆመ ፕሮጀክት ... እንደገና መነሳት ይችላል::

የጀመርከውን ነገር የመጨረስን ስኬት ለመለማመድ የሚከተሉትን ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ትችላለህ::





# መጨረሻውን አይተህ ጀምር

መጨረሻውን አይተህ ለመጀመር የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል:: "ይህ የምጀምረው ነገር ሲያልቅ ውጤቱ ምን እንዲመስል ነው የምፈልገው?" ይህንን ጥያቄ መመለስ ለመጨረስ ቆርጠህ እንድትጀምር ውስጥህን የሚያነሳሳ እይታን ይሰጥሃል:: በተጨማሪም፣ የአንድን ነገር ፍጻሜውን በማየት ጽኑ በሆነ አላማ እንድትጀምረውና ጠንክረህ እንድትቀጥል ይደግፍሃል:: የአንድ ነገር ጅማሬውን ብቻ ሳይሆን ፍጻሜውንም ቁልጭ ባለ መልኩ ስታየው በነገሩ የማመንህንና ያለማመንህንም ነገር እንድትወስን ያደርግሃል:: ለመጀመር ያለህ ጉጉት ይህንን የውስጥ ፍላጎት ሊጋርድብህ ይችላል:: የፍጻሜውን ስእል ግን በአእምሮህ አይተህ ስትጀምር ጉጉትህ በጅማሬው ላይ ብቻ መሆኑ ይቀርና ወደ ፍጻሜው ላይ ይሆናል:: ለመጀመር ካለህ ጉጉት ይልቅ ለመጨረስ ያለህ ጽኑ ፍላጎት ካልበለጠ የመጨረስህ ጉዳይ አጠራጣሪ ነው::

*"ወደ የት እንደሚሄድ ለሚያውቅ ሰው ይህቺ አለም መንገዱን ትለቅለታለች" – Ralph Waldo Emerson*

ወደ የት እንደምንሄድ የመንገዳችንን ፍጻሜ በግልጽ አይተን ካልተነሳን የመጣው እንቅፋት ሁሉ ያስቆመናል:: ምክንያቱም በተቋቋመን እንቅፋት ምክንያት የቆምንበትን ስፍራ እንደ ፍጻሜአችን የመቁጠር ዝንባሌ ስላለን ነው::

መጨረሻውን በአይነ-ኅሊናችን አይተን ከተነሳን ግን በፊታችን የሚደነቀሩትን እንቅፋቶች ማለፍ እንዳለብን አምነን ነው የምንጀምረው - በዚህም ሆነ በዚያ ብለን ጥረን ስናልፋቸው ራሳችንን እናገኘዋለን:: ግብ የሌለው ሰው ኳሱን ወደ የትም አቅጣጫ ቢመታው፣ ኳሱ የደረሰበትን ስፍራ እንደ ግብ የማየት ዝንባሌ ይኖረዋል:: ኢላማ የሌለው ሰው በየትም አቅጣጫ ቢተኩስ በተኩሱ ድምጽ ከመደሰትና የተኮሰው



Scanned with CamScanner

“የምትሄድበትን ካላወቅህ የትኛውም መንገድ ይወስድሃል” የሚልን መልእክት ተቀብሎ፣ “መልእክቱ ገብቶኛል” በሚል ዝምታ ተዋጠ::

*“ቁም ነገሩ ከየት እንደመጣህ አይደለም፣ ዋናው ቁም ነገር ወደ የት እንደምትሄድ ማወቅህ ነው” – Brian Tracy*

ብዙ ሰዎች በደመ-ነፍስ ነው የሚኖሩት:: ከየት ተነስተው ወደ የት መሄድ እንዳለባቸው በቅጡ አያውቁትም:: ወደ የት እንደሚሄዱ ማወቅ በሕይወት ላይ ያለውን ተጽእኖ በፍጹም አስበውት አያውቁም:: የግብ ጉዞ የምርጫ ጉዞ ነው - “የትኛውን ጎዳና ብመርጥ ወደ ዋናው የሕይወቴ አላማና ራእይ ያደርሰኛል” የሚል ምርጫ! ግቡን በቅጡ ያላወቀ ሰው የመጣውን ያስተናግዳል፣ ወደተከፈተለት ይገባል፣ ጊዜአዊ ደስታን በሰጠው ነገር ላይ ጊዜውን ያባክናል:: ሕይወት በምርጫ የተሞላች ነች:: ጠዋት በስንት ሰአት ከመኝታዬ መነሳት እንዳለብኝ ከምወስነው ውሳኔ አንስቶ ማታ በስንት ሰአት ወደመኝታዬ መሄድ አለብኝ እስከሚለው ድረስ የምንመርጠው ምርጫና የምንወስነው ውሳኔ በአላማችን ላይ ጣልቃ ይገባል::

ስለዚህም፣ ስኬት የሞላበት ሕይወትን ለመኖር ከፈለግህ፣ ግብን በማውጣት ጥበብ የበሰልክ ልትሆን የግድ ነው:: የሚከተሉትን እውነታዎች አሰላስላቸው::

## ግብህንና ራእይህን አጣጥማቸው

ግብህ ረጅምና የተንዛዛ ከሆነ ከዋናው ሕልምህ ጋር የመጣጣሙን ነገር መመዘን ያስቸግርሃል:: ስለዚህ በቅድሚያ የምታወጣቸው ግቦች አጭርና ግልጽ ይሁኑ:: ግብህ ምንነቱና ውጤቱ ሊመዘን የማይችል ከሆነ አሁንም ከዋናው ራእይህ ጋር የመጣጣሙን ሁኔታ መመዘን ያስቸግርሃል:: ግብህ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ትጋትህንና ጽንአትህን የሚፈትን ወይም የሚወጥርህ፣ ቀላል ከመሆኑ የተነሳ ደግሞ ሊደረስበት የሚችል ሊሆን ይገባዋል:: አስታውስ፣ የጥቃቅን ግቦችህ መሳካት ነው የዋናውን ራእይህን ፍጻሜ





የሚወስነው:: በመጨረሻም፣ ራእይህ የጊዜ ገደብ ካለው ግቦችህም እንዲሁ ሊኖራቸው ይገባል:: ጥቃቅን ግቦችህ ተጠራቅመው ታላቁን ራእይህን የሚሰሩት ከሆነ፣ የእነዚህ ጥቃቅን ግቦችህ የጊዜ ገደብ መስመር ከያዘ ራእይህ መስመር የማይዝበት ምንም ምክንያት የለም:: ሂደቱ ውስብስብ አይደለም - ራእይህ ግልጽ ሲሆን፣ ወደዚያ ራእይ የሚያደርሱህን ግቦች ማውጣት ቀላል ይሆናል:: የእነዚህ ግቦች ጥርቅምና መገጣጠም የራእይህን ስእል ካልሳሉት እንደገና ልታስብበት ይገባል::

*“ብዙ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው አሳ እንዳልሆነ ሳይገባቸው እድሜ ልካቸውን አሳ ሲያጠምዱ ይኖራሉ” –Henry David Thoreau*

“ግቦችህን ከራእይህ አንጻር ያለመቃኘትህ ትልቁ ክስረት የሰዓት ክስረት ነው:: በዚህ ምድር ላይ ለማንኛውም ነገር የምትከፍለው በሰዓት ወይም በጊዜህ እንደሆነ አትርሳ:: ለምሳሌ፣ ወደ ራእይህ የማይወስድን ነገር ስትከታተልና ለመገንባት ከምትፈልገው ነገር ጋር ምንም የማይገናኝ ቁሳቁስ ስትለቃቅም አንድ አመት ብታሳልፍ የከፈልከው ገንዘብን አይደለም ጊዜን ነው:: ሁኔታውን በዚህ መልኩ አስበው - መስሪያ ቤትህ የሚከፍልህ የመስሪያ ቤትህን ችግር ለመፍታት ባሳለፍከው ሰዓት መጠን ነው:: እነዚህን ሰዓቶችህን በዚያ መስሪያ ቤት ማሳለፍና መጠቀም እንዳቆምክ ክፍያውም እንዲሁ ይቆማል:: የገንዘብህን ሁኔታ የሚጫወተው ጊዜህ ነው:: ግብ የማውጣት ጥቅሞች ሲጨመቁ፣ ጊዜን በአግባቡ ወደመጠቀም እውነታ ይወርዳሉ:: ጊዜን የከሰረ፣ ገንዘብ እንደከሰረ ሊቆጥረው ይገባዋል::

ከዚህ ሕግ የተነሳ ነው ከተማችን ውስጥ ብዙ ሕዝብ ወዲህና ወዲያ ሲተራመስ የሚታየው:: መፍትሄው - ከራእይ አንጻር የተቃኙ ግቦችን በጥንቃቄ ማውጣት!

## በየቀኑ ወደ ግብህ የሚያደርስህን አንድ ነገር አድርግ

የራእይና የግብ ጉዳይ በወር አንድ ጊዜ ወይም ደግሞ ሲመችህ እያሰብከው የሚደረስበት ጉዳይ አይደለም:: አምስቱም የስሜት ህዋሳቶችህ ካለማቋረጥ መሳተፍ አለባቸው:: ግብህን ውስጥህ ካለማቋረጥ ማየት አለበት፣ በእጆችህ በመተግበር መዳሰስ አለብህ፣ ስለግብህ ለማንነትህ በመንገር ራስህን ማስታወስ አለብህ፣ የግብህን ጣፋጭነት ማጣጣም አለብህ፣ የግብህን መልካም ጠረን ማሽተት አለብህ:: ይህ ደግሞ ሊሆን የሚገባው በየቀኑ ነው:: ወደመኝታህ ከመሄድህ በፊት ግብህን አስበህ ተኛ:: ይህንን ማድረግህ ውስጠ-ኅሊናህ (subconscious mind) ግቡን አብስሎት እንዲያድር ያደርገዋል:: ጠዋት ወደተግባርህ ስትሰማራ ግብህን በቅርብ በምታይበት ስፍራ ለጥፈው፤ ውሎህን ከግብህ ጋር አድርግ:: ይህንን ስታደርግ ግብህ ከመድረስ ውጪ ምንም ምርጫ አይኖርህም::

*"የምትፈልገውን ነገር ካልተከታተልከው አትጨብጠውም:: ካልጠየክ መልሱ ሁልጊዜ የአምቢታ ነው:: ወደፊት ካልተራመድክ ዘወትር ራስህን ባለህበት ታገኘዋለህ" – Nora Roberts*

ባለህበት ቆመህ ወደ አንድ መድረስ ወደምትፈልግበት ስፍራ ለመድረስ መመኘት ሞኝነት ነው:: ወደ አላማህ የሚያደርስህ ነገር ያለው ሰዎች ጋር ከሆነ፣ ያንን ከሰዎች ለማግኘት የፈለከውን ነገር ለማግኘት የግድ መጠየቅ አለብህ:: ካልጠየክ፣ የእምቢታን መልስ የማግኘትህ እድል መቶ በመቶ ነው፣ ምክንያቱም ሰዎች ስላልተጠየቁ የእሺታን መልስ መስጠት አልቻሉምና ነው:: ለመጠየቅ ብትደፍር ግን እምቢ የመባልህን ሁኔታ በግማሽ ትቀንሰዋለህ - እምቢ ወይም እሺ የመባልህ እድል ግማሽ ግማሽ ይሆናል::

ሰዎች ሁኔታዬን አይተው ራሳቸው ይህንና ያንን ያደርጉልኛል ብሎ ማሰብ ልብን ለኃዘን ማዘጋጀት ነው:: ሰዎች ሃሳባቸውን ሁሉ የሚወስድ የራሳቸው ሩጫ አለባቸው::





ከዚያም በተጨማሪ፣ ሰዎች አንተን አይተው ምን አይነት እይታ ሊኖራቸው እንደሚችል አታውቅም:: ሁኔታህ የተሳካለትና የተመቸው ሰው እንደሆንክ አመላካቿቸው ይሆናል:: ስለዚህ፣ ስራ፣ ጠይቅ፣ አንኳኳ፣ ገንባ፤ ወደ ራእይህ በየቀኑ አንድን እርምጃ ተራመድ::

## አደራረግ ላይ ግትር አትሁን

አንዳንድ ሰዎች ስለግባቸውና ስለዋናው ራእያቸው ከሚጨነቁት ይልቅ ወደዚያ ግብ ለመድረስ ስለሚጠቀሙበት መንገድ ይጨነቃሉ:: የብዙ ኮሚቴ ክርክር ስለዋናው ራእይ ሳይሆን እዚያ ለመድረስ ስለሚወሰደው እርምጃ ነው:: ራእይህና ፍጻሜህ ወደ አንድ ከተማ የመሄድ ከሆነ ምናልባት ምርጫህ ብዙ ነው:: በአየር፣ በግል መኪና ወይም ደግሞ በሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ:: በዚህም ሄድክ በዚያ መድረስ በምትፈልግበት የቀን ገደብ በሰላም መድረስህ ነው ቁም ነገሩ እንጂ በምን መልኩ እንደደረስክ አይደለም:: የመድረስህን ጉዳይ ካለህ የጊዜ ገደብና ካለህ የኢኮኖሚ ብቃት ጋር አመዛዝነህ ሂድ - ብቻ ሂድ! በምን ልሂድ የሚለውን ለመወሰን ስታወጣና ስታወርደ ከአላማህ አትቅር:: ይህንን መመሪያ በተለይም በማህበር በሚሰሩ ስራዎች ላይ ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው:: "ግባችን ለመድረስ የሚበጀን ጎዳና የቱ ነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲከራከሩ የግቡ የጊዜ ገደብ የሚቃጠልባቸው ኮሚቴዎች ስንት ናቸው?

*"ግቡ አልደረሰ ያለ ሲመስልህ መቀየር ያለብህ ግቡን ሊይደለም አደራረግህን እንጂ" - Unknown Source*

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው አንዳንድ ጊዜ አንድ ግብ ጋር ለመድረስ የምንከተለው ጎዳና ከባድ ሲሆን ራእይንና ግብን መቀየር ያምረናል:: ይህ ግን ሊሆን አይገባውም:: መቀየር ያሉብን የአደራረግን ስልት ነው:: አንዳንድ ሰዎች አንድ ስልት ብቻ የማስተናገድ ዝንባሌ



Scanned with CamScanner

Wallenda) ነው:: ካርል ብዙ ድፍረት የሚጠይቁ ነገሮች በማድረግ የታወቀ ሰው ነው - የፍርሃት ቃል አውጥቶ አያውቅም:: በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1978 ዓ.ም በሳንዋን፣ ፖርቶሪኮ ውስጥ በሚገኙ ሁለት የባለ አስር ፎቅ ህንጻዎች ላይ በተወጠረ ገመድ ላይ ለመራመድ ሙከራ አደረገ:: ያቺ ሙከራ የዚህ ሰው የሕይወት መጨረሻው ነበረች - ተከሰከሶ የሞተበት ቀን:: ከሞተ በኋላ ሚስቱ ስትናገር እንዲህ አለች፤ "ይህንን ከመሞቱ በፊት ያደረገውን የመጨረሻ የገመድ ላይ ርምጃ ከማድረጉ በፊት ለሶስት ወራት ሙሉ አለወትሮው ወሬው ሁሉ የመውደቅ ፍርሃት ነበር:: የፍርሃትን ሃሳብ ሲያስብ የመጀመሪያው ጊዜ ነው:: እንደ እኔ አመለካከት ሃሳቡን ሁሉ የጣለው በገመዱ ላይ በመራመድ ላይ ሳይሆን ባለመውደቅ ላይ ነበር::"

*"ጀግንነት ማለት የፍርሃት አለመኖር ማለትሳይሆን ፍርሃትን አጥብቆ በመቋቋም የመቆጣጠር ብቃት ማለት ነው" - Mark Twain*

የምትፈራው ጤና ቢስ ነገር ተስፋ ከምታደርገው መልም ነገር ይልቅ ፈጥኖ የመምጣት ባህሪይ እንዳለው አስተውለህ ታውቃለህ? ይህ የሚሆነው እድልህ እንደዚያ ስለሆነ አይደለም፤ በዙሪያህ ያለው ነገር መልካሙን ህልምህን ሳይሆን ፍርሃትህን የሚመግቡ መረጃዎችን የማቅረብ ዝንባሌ ስላለው ነው::

ፍርሃትህን መጋቢው ብዙ ነው:: የፈሪውና "የአጉል ጠንቃቃው" ወሬ፤ የምእራቡ የዜና አገልግሎት የዝገባ ትኩረት ... የፍርሃት ምግቡ ብዙ ነው::

ፍርሃት እንዲህ ይልሃል ...

- አትመልከት - አንድ ነገር እንዳታይ!
- አታድምጥ - አንድን ነገር እንዳትሰማ!
- አታስብ - አንድ ድምዳሜ ላይ እንዳትደረስ!
- አትወስን - ስህተት እንዳትሰራ!





- አትራመድ - እንዳትወድቅ!
- አትኑር - እንዳትሞት!
- አትማር - ፈተና እንዳትወድቅ!
- አትውደድ - እንዳትጎዳ!

በሕይወትህ ልታነግስ የምትችለው ስሜት አንዱን ብቻ ነው - የፍርሃትን ወይም የመኖር ድፍረትን:: አንዱ እንዲነግስ ስትፈቅድለት ለሌላኛው የባርነት ትእዛዝን እያስተላለፍክ ነው:: ፍርሃት ሲነግስ የመኖር ጣእም ይጠፋል:: ይህ እንዳይሆን የሚከተሉትን ጠቃሚ ምክሮች ማሰብ ትችላለህ::

## ፍርሃትህን ለየው

ሁለት አይነት የፍርሃት አይነቶች አሉ፡- የተመዛዘነ (Rational) ፍርሃት እና ያልተመዛዘነ (Irrational) ፍርሃት:: የተመዛዘነ የተሰኘው ፍርሃት መረጃን የተመረኮዘና የአንድ ነገር አደገኛነት እውን ሲሆን የሚመጣ የፍርሃት አይነት ነው:: ለምሳሌ፣ በመዝናኛው ስፍራ ባለው ሳር ውስጥ መርዛማ እባብ ካለ ያንን መፍራት የተመዛዘነ ፍርሃት ነው:: ይህ አይነቱ ፍርሃት ተጨባጭ ሁኔታንና መረጃን ተመርኩዞ የመጣ ፍርሃት ነው:: ለዚህ አይነቱ ፍርሃት ያለው ብቸኛ መፍትሄ አደጋው እንዳይደርስ የሚቻለውን ካደረጉ በኋላ ቀና ብሎ መኖር ነው:: ሌላኛው የፍረሃት አይነት ያልተመዛዘነ ፍርሃት ነው:: ይህ፣ እንዲሁ በሆነ ባልሆነውና ምንም ተጨባጭ ነገር ባልተገኘበት ሁኔታ የነገሰ የፍርሃት አይነት ነው:: አንዳንድ ሰዎች የሚፈሩትን እንኳ ምን እንደሆነ ሳያውቁት እንዲሁ በጥርጣሬ ፈሪዎች ናቸው:: የፍርሃቱ አይነት ይህም ሆነ ያኛው፣ የምንሰጠው ምላሽ ወሳኝ ነው::

*"ለመግባት የፈራኸው ዋሻ የምትፈልገውን ሃብት ይዞ ይሆናል" – Joseph Campbell*



Scanned with CamScanner

ብዙ ጊዜ መልካም ፍሬ የሚገኝባቸው ነገሮች ድፍረትን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው:: የኢንቨስትመንቱን ጉዳይ ስታስበው፣ ብከስርስ የሚል ስሜት ይለቅብሃል:: ምርጫህ ሁለት ነው - ፍርሃትህን በማሸነፍ የኢንቨስትመንት ጎዳና ውስጥ በጥንቃቄ መግባት ወይም ደግሞ በፍርሃት በመታሰር ባሉበት መርገጥ:: የመማርን ነገር ስታስብ፣ ፈተና ብወድቅና ብዋረድስ የሚል ስሜትን ሳይሰጥህ አያልፍም:: አሁንም ምርጫህ ሁለት ነው - ፍርሃትን በማስተናገድ ባለህበት የትምህርት ደረጃ መቅረት ወይም ደግሞ "ብወድቅ እንኳ እነሳለሁ" በማለት ለእውቀት ራስህን መከፈት:: የቱ ይሻልሃል? አንዳንድ ሰዎች የእንዲህ አይነቱን የፍርሃት ስሜት ስለማይፈልጉት ስለጉዳዩ ማሰብን ያቆማሉ:: ስለ አዲስ ነገር ማሰብ ማቆም ማለት ደግሞ ስለ ስኬት ማሰብ ማቆም ማለት ነው:: እውነታው ግን ይህ ነው፣ ፍርሃትን በመሸሽና በመደበቅ አታሸንፈውም፣ በመጋፈጥ እንጂ:: ፍርሃትን በመደበቅ ስታልፈው አሸነፍከው አይባልም፣ ለሌላ ጊዜ አስተላለፍከው እንጂ! ፈጠነም ዘገየም ያንን ፍርሃት መጋፈጥህ አይቀርም፣ ስለዚህ አሁኑኑ ፍርሃትን ተጋፍጠህ ማሸነፉ ይመረጣል::

## መፍራትን አትፍራው

እንደ ፍርሃት፣ ድንጋጤና ስጋት አይነት ስሜቶች ሰው ከአደጋ እንዲጠነቀቅ ከፈጣሪው የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው:: እነዚህ ስሜቶች በአግባቡ ልንጠቀምባቸውና ከአደጋ ልንጠበቅባቸው ሲገባን ለአንዳንድ ሰዎች የኑሮ ዘይቤ ሆነዋል:: የመውደቅ ፍርሃት፣ የመከሰር ፍርሃት፣ ያለመወደድ ፍርሃት፣ ብቻ የመቅረት ፍርሃት፣ ... ጣጣችን ብዙ ነው:: በፍርሃት ስንወረስ፣ ሕይወታችንን በራእይ መምራት እናቆምና ለፍርሃት ምላሽ በመስጠት መምራት እንጀምራለን:: ከአንዱ ራእይ ወደሌላኛው በማለፍ ሕይወትን "ልናጣቃት" ሲገባን የመጣው ሁሉ የኑሮ ገጠመኝ የሚያጠቃን ቋሚ ኢላማዎች እንሆናለን:: ቆመን ለመጣው ወይም የመጣ ለመሰለን ጥቃት ምላሽ በመስጠት ጊዜአችንን እናባክናለን:: ይህ ሲሆን የቆመ ኢላማ ሆንን ማለት ነው:: በተቃራኒው





ከአንዱ ግብ ወደሌላኛው በአላማ የምንንቀሳቀስ ሰዎች ስንሆን አይኖቻችን ከችግሩ ላይ ይነሱና መፍትሄው ላይ ማረፍ ይጀምራሉ::

*የፍርሃትህ ጥልቀት አእምሮህ የፈቀደለት ያህል ነው" - Unknown Source*

ፍርሃት በሕይወትህ ብቅ ጥልቅ ማለቱ አያስፈራህ:: በዚያ ፍርሃት ምክንያት ግን መንቀሳቀስ እስኪያቅትህ ድረስ እንዳትታሰር ፍራ:: ማንኛውም ሁኔታ አንተን የማስፈራራት ሙከራ የማድረግ ሙሉ መብት አለው:: አንተ ካልፈቀድክለት ግን ሊያስፈራራህ አይችልም:: ትፈራለህ፣ ፈሪ ግን አይደለህም:: "በፍጹም አልፈራም" ብለህ ካሰብክና ከተናገርክ ከፍርሃት የተደበቅህ ሰው እንደሆንክ አመልካች ነው:: በሌላ አባባል፣ የፍርሃት ስሜት እንዳይመጣ መከልከል አትችልም፣ ይህንን ስሜት ለማስተናገድ የተፈጠረ ማንነት ስላለህ:: ሆኖም፣ የፍርሃትን ጥልቀትና በአንተ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት የመወሰን ሙሉ መብትም ሆነ ብቃት አለህ::

## ንግግርህን ቃኝ

የምትሰጋበት ነገር በሕይወትህ ካለ ስለዚያ ጉዳይ ከራስህ ጋርም ሆነ ከወዳጆችህ ጋር መነጋገርህ አይቀርም:: መናገርህ መልካም ሆኖ ሳለ፣ የምታወጣቸው ቃላት ግን ወሳኝ መሆናቸውን አትዘንጋ:: አንዳንድ ጥናቶች እንደሚነግሩን ከሆነ አእምሮአችን የምንናገራቸውን ፍርሃት-ተኮርና አሉታዊ ነገሮች ለቅሞ የማከማቸት ዝንባሌ አለው:: ለምሳሌ፣ በዚህ ንግድ "አልከስርም" ከማለት ይልቅ በዚህ ንግድ "አተርፋለሁ" የሚለውን አባባል መልመድ ጠቃሚ ነው:: የመጀመሪያው አባባል "ከስረት" የሚለውን አሉታዊ ሃሳብ በአእምሮህ መዝግቦ አልፎአል:: ሁለተኛው ግን የመዘገበው "አተርፋለሁ" የሚለውን ነው:: አእምሮህ ሰውነትህን የሚያዝዝ መቆጣጠሪያ ማእከል እንደመሆኑ መጠን፣ ለማስተናገድ የሚያስተላልፈው የመዘገበውን ነገር ነው:: በአእምሮህ ውስጥ ጤናማ ነገር አጠራቅም::



Scanned with CamScanner

*"ተግባርህን ከንግግርህ ጋር፣ ንግግርህን ደግሞ ከተግባርህ ጋር ቃኛቸው" – William Shakespeare*

ከአንደበትህ የምታወጣቸው ቃላት መራመድ ከምትፈልገው እርምጃና መሆን ከምትፈልገው የውስጥህ እይታ ጋር መጣጣማቸውን እርግጠኛ ሁን:: ሰው የሚበላው የምግብ አይነት በአካሉ ላይ እንደሚንጸባረቅ ሁሉ፣ የአንተም ማንነት የምትሰጠውን ምግብ ወደመሆን የመምጣት ዝንባሌ አለው:: ለራስህ ፍርሃትን፣ ጥርጣሬን፣ ድህነትን፣ መውደቅንና መገፋትን ንገረው፣ ከእነዚህ ነገሮች አታልፍም:: ለራስህ ግን ጤናማ፣ የድልና የስኬት ሃሳቦችን መናገር ስትጀምር ራስህን በዚያ መልኩ ማየትና ማስተናገድ ትጀምራለህ:: ይህ ሁኔታ በስኬታማነትህ ላይ ታላቅ ስፍራ አለው::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ፍርሃትን የማሸነፍ ጥበቦች:-

1. ፍርሃትህን ለየው
2. መፍራትን አትፍራው
3. ንግግርህን ቃኝ

*በሕይወትህ ልታነግስ የምትችለው ስሜት አንዱን ብቻ ነው – የፍርሃትን ወይም የመናር ድፍረትን::*





# 20

# ስለ ተፈተንክ ሳይሆን ስለ ተዘጋጀህ!

## የመዘጋጀት ቁልፍ



ከደረስንበት ሁኔታ የተሻለ እያለ የደረስኩበት ይበቃኛል በማለት መሰከን ለምንድን ነው? ለወርቅ መሮጥ ሲቻል ለብርና ለነሃስ መሮጥ ለምንድን ነው? ባለን ከረካን ወዳልደረስንበት የተሻለ ነገር ለመራመድ ፈቃዱም አይኖረን:: የእምቅ ብቃታችን ጠላት ምንድን ነው? የለመድነው፣ የተመቸን፣ የማያስለፋን፣ ሁሉም ያደረገው፣ "መኖር ከተቻለ ምን አስለፋኝ" ያሰኘን አይደለምን? ነገር ግን፣ ከዚህ የተሻለ አለ!!! ራስህን ካዘጋጀህ፣ ብዙም ሳትቆይ አሁን ከደረስክበት የተሻለ ደረጃ እንዳለ ማየት ትጀምራለህ:: ሰው ከጻፈው አንተ ማንበብ ትችላለህ፣ ሰው ካሰረው አንተ መፍታ ትችላለህ፣ ሰው ከደበቀው አንተ ማግኘት ትችላለህ::

አንዲት አስተማሪ ከዚህ በፊት ለተማሪዎቿ ብዙ ጊዜ ፈተናን ፈትናቸው ታውቃለች:: አንድ ጊዜ ግን ከዚህ በፊት አድርጋ የማታውቀውን ነገር ለማድረግ ወሰነች:: ለፈተና ተዘጋጅተው የፈተናው ወረቀት እጃቸው እስኪገባ የሚጠባበቁትን ተማሪዎች እንዲህ አለቻቸው፣ "ይህንን ፈተና ሳልፈተን የ"B" ውጤት ቢሰጠኝ በደስታ እቀበላለሁ የምትሉ ተማሪዎች ስማችሁ እየተመዘገባችሁ አሁኑኑ ከዚህ ክፍል መውጣት ትችላላችሁ:: ፈተናውን መፈተንና "A" ለማግኘት ስለተዘጋጀሁ ጥረት አደርጋለሁ የምትሉ ተማሪዎች



Scanned with CamScanner

እነሱ ከወጡ በኋላ ፈተናውን ትወስዳላችሁ"፡፡ ይህን ሃሳብ እንደተናገረች ከተማሪዎቹ አብዛኛዎቹ ስማቸውን እየተመዘገቡ ክፍሉን ጥለው ውልቅ አሉ፡፡ እጅግ የተገረመችው አስተማሪ፣ አሁንም መውጣት የሚፈልግ ተማሪ ካለ አንድ የመጨረሻ እድል ሰጠች፡፡ ይህንን የመጨረሻ እድል ገና ከአንደበቷ ከማውጣቷ ከአንድ ተማሪ በስተቀር ተማሪው ሁሉ ስሙን ተመዝግቦ አንድ በአንድ ተፈተለከ፡፡ መውጣት የፈለጉት ተማሪዎች ሁሉ መውጣታቸውን ካረጋገጠች በኋላ "A" ለማግኘት እፈተናለሁ ብሎ የተዘጋጀውን ብቸኛ ተማሪ አንድን ደስ የሚያሰኝ ዜና አበሰረችው፣ "አንተ አሁኑኑ፣ ፈተናውን ሳትፈተን "A" ተሰጥቶሃል - ፈተናውን ስለተፈተንክ ሳይሆን ስለተዘጋጀህ፡፡ "A" የሚገባህ ያንን ለማግኘት የቆረጠ ማንነት ስላለህና ለዚያም ውስጥህን ስላዘጋጀህ ነው!!!"

*"ለአማካኝና ለመካከለኛ ውጤት ለሰከኑ ሰዎች አማካኝና መካከለኛ ውጤት እንደ ግሩም ውጤት ይቆጠራል" – Unknown Source*

ማወቅ ሲቻል ሰው ባለማወቅ ለመኖር ሲመርጥ ያስገርማል፡፡ሙቶ ማግኘት ሲቻል ሰው በሃምሳ መስከኑ ግር ይላል፡፡ ከዚህ የተሻለ ማድረግ ስችል እስካሁን ባደረኩት የመስከኔ ምንጩ ምን እንደሆነ አግኝቼው እስከቀርፈው ድረስ ሕይወት ባሉበት መርገጥ ይሆናል፡፡

መድረስ የምትችለው እስካሁን ከደረስክበት ደረጃ ያለፈ እንደሆነ በምን ታውቃለህ? ማወቅ የምትችለውስ እስካሁን ካወከው እውቀት የላቀ እንደሆነ ምን ማረጋገጫ አለህ? ማንነትህን መድረስ እስከሚችልበት ደረጃ ድረስ ወጥረኸዋል? በአማካኝ ውጤት ለማለፍ ነው የምትሄደው ወይስ የብቃትህ ጥግ ድረስ ለመድረስ? አሁን ያለህበት የትምህርት ደረጃ ላይ ለምን አቆምክ? አሁን የደረስክበት ደረጃ ላይስ ለምን ሰከንክ? ሕይወት ግሩም የሆኑ እድሎችን የምትሰጠው ለተዘጋጁት ነው፡፡ ስኬታማዎቹ ሰዎች እድለኞች ስለሆኑ አይደለም ሁኔታው የሚመጣላቸው፣ ስለተዘጋጁ እንጂ፡፡ የስራ እድል ለእድለኞች አይደለም ተምረው ለተዘጋጁ እንጂ! የሩጫ ውድድር የሽልማት እድል





ለእድለኞች አይደለም፣ በሩጫ ልምምድ ለተዘጋጁ እንጂ! በአንድ ነገር ራስህን ብቁ በማድረግ ስትዘጋጅ መልካም እድለኛ ለመሆን ወሰንክ ማለት ነው፡፡

የተዘጋጀህ ሰው ሆነህ እንዳትገኝ ምናልባት የሚከተሉት እንቅፋቶች ተደንቅረውብህ እንዳይሆን ራስህንና ሁኔታህን ገምግመው፡፡

## ስንፍና

"ስንፍና ማለት ሳይደከመን የማረፍ ልማድ ነው" ይባላል - እውነት ነው! ስንፍና ማለት አብቃቅቶ ለመኖር የሚቻልበት ደረጃ ድረስ ከሄዱ በኋላ ማቆም ማለት ነው፡፡ እናልፋለን ነገር ግን በጥቂት ነጥብ ነው የምናልፈው፡፡ እንሰራለን፣ ነገር ግን ከመስሪያ ቤት የመውጫ ሰዓታችንን እያየን ነው የምንሰራው፡፡ ስንፍና ማለት ያላደረግናቸውን መልካም ነገሮች ያላደረግንበትን "በቂ ምክንያት" ይዞ መቀመጥ ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው እንዲህ ሲል እውነትን ተናገረ፣ "ስንፍና እጅግ ቀርፋፋ ከመሆኑ የተነሳ ድህነት የተባለ ኤሊ ተከታትሎ ይደርስበታል"፡፡ ስንፍናህን ወደ ትጋት በመለወጥ ለተሻለ ነገር ለመስራት ቁርጠኝነት ከሌለህ አንደኛህን "ስኬት" የሚለውን ቃል ከሕይወትህ መዝገበ-ቃላት ማውጣቱ ይመረጣል፡፡

*"ከረምት መጥቶ በበጋው ወራት ምን ስታደርግ ከረምክ ብሎ የሚጠይቅህ ጊዜ ይመጣል" – Henry Clay*

ስንፍናን ለይቶ ለማስወገድ አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች መካከል አንዱ ውጤቱ ወዲያውኑ ስለማይታወቅ ነው፡፡

የትናንትና የስንፍና ዘራችንን ነው ዛሬ የምንበላው፡፡ የዛሬውን ደግሞ ወደፊት! የዛሬ ስንፍናችን ሁኔታ ዛሬውኑ የሚያንገበግበን ቢሆን ኖሮ እንታረም ነበር፡፡ ጉንዳኖች የበጋውን ሙቀትና ጸሐይ ቢደስቱበትም እንኳ፣ ለክረምት የማጠራቀማቸውን ዲሲፕሊን



Scanned with CamScanner

ግን በፍጹም አይዘነጉም:: አለዚያ ግን የሚከተላቸውን ያውቃሉ:: ትጋት ለዛሬ ሲያበላ ታይቶ አይታወቅም:: የትጋት ፍሬው የሚታወቀው ነገ ነው:: ስንፍናም እንዲሁ:: ስለዚህ፣ ዛሬ ተጫውተህ ነገ ከምትሰራ፣ ዛሬ ሰርተህ ነገ ብትጫወት ይሻልሃል:: ዛሬ በልተህ ነገ ከምትከፍል፣ ዛሬ ከፍለህ ነገ ብትበላ ይሻለሃል::

## ግድ የለሽነት

ግድ የለሽነት ማለት አንድ ነገር ሆነ አልሆነ ምንም ስሜት ሳይሰጠን ሲቀር ማለት ነው:: ቀድሞ በትጋት ያደርገው የነበረውን ነገር አሁን ችላ የሚል ሰው ግድ የለሽነት እንደተጫጫነው አመልካች ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የንጽህና ተቃራኒው ቆሻሻ አይደለም፣ ግድ የለሽነት እንጂ:: የብልጽግና ተቃራኒው ድህነት አይደለም፣ ግድ የለሽነት እንጂ:: የፍቅር ተቃራኒ ጥላቻ አይደለም፣ ግድ የለሽነት እንጂ:: የማግኘት ተቃራኒው ማጣት አይደለም፣ ግድ የለሽነት እንጂ:: የ "A" ተቃራኒው "B" አይደለም፣ ግድ የለሽነት እንጂ:: ከግድ የለሽነት ተላቅቀን ለአንድ ውጤት ተግተን ብንሰራ ያንን ውጤት ማግኘታችን አይቀርም:: የብዙ አለመሳካታችን ምንጩ ግድ የለሽነት ነው:: ለውጤት ግድ ካለህ፣ ያው አለህ ነው - ማግኘትህ አይቀርም:: ግድ ያለህ ነገር ላይ ልቦናህን መጣልህ ስለማይቀር ማለት ነው::

*"ከግድ የለሽነት የተነሳ አንድ ሰው በእርግጥም ሳይሞት የሞተ ሊሆን ይችላል" - Elie Wiesel*

ለአንድ ሰው ከግድ የለሽነት የበለጠ ድንዛዜን ሊሰጠው የሚችል ነገር ምን አለ? ድንዛዜ ደግሞ ሃውልት ያደርግሃል፤ አለህ ግን የለህም:: ግድ የለሽነት ለሁኔታዎች ስሜት የሌለህና ምላሽ የማትሰጥ ሰው እንድትሆን ያደርግሃል:: ባል ለሚስቱና ለልጆቹ ግድ የለሽ ሲሆን፣ ሚስት ለቤቷ ሁኔታ ግድ ሳይሰጣት ሲቀር፣ ሰራተኛ በመስሪያ ቤቱ ላለው ወሳኝ ነገር ግድ የለሽ ሲሆን፣ መሪ ለሚመራው ሕዝብና ተቋም ግድ የለሽ ሲሆን፣





ሕዝብ ለሃገሩ እድገት ግድ የለሽ ሲሆን፣ ... አንድ ሕብረተሰብ ወለሉ ድረስ ወደታች ወረደ ማለት ይህ ነው::

ለስኬት የተዘጋጀ ማንነት እንዲኖርህ ከፈለግህ ግድ የለሽነትን በማሸነፍ ውስጥህን በጋለ ስሜት ሙላው:: የምትከታተላቸውንም ነገሮች በጋለ ስሜት ተከታተላቸው::

## የልማድ ጉድለት

አንዳንድ ሰዎች ስኬታቸውን በአንድ ቀን ባስመዘገቡት ጊዜአዊ ድል ይወስኑታል:: ስኬት ግን ልማድ እንጂ የአንድ ቀን ክስተት አይደለም:: ስኬት የሚመጣው ከልማድ ነው፤ ደግሞና ደጋግሞ አንድን ነገር ከማድረግ ልማድ:: ይህ እይታችን ሲስተካከል በአንድ ጊዜ የአለመሳካት ክስተት አንረበሽም፣ በአንድ ጊዜ የስኬት ክስተትም በመኩራራት አንዘናጋም:: ስኬት የየቀኑን የሕይወት ጥቃቅን ፍልሚያዎች ከማሸነፍ ያለፈ ነው:: ራስን በመግዛትና በማሰልጠን፣ መልመድ የሚገባንን ለመልመድና ማወቅ የሚገባንን ለማወቅ የመወሰን ጉዳይ ነው:: ዛሬ በቀላሉ የምታደርጋቸው ነገሮች ትናንት የተለማመድካቸው ነገሮች ናቸው:: ዛሬ የምትደጋግማቸው ነገሮች ደግሞ ነገ ልማድ ይሆኑና ለሌላው የሚያታግለውን አንተ በቀላሉ አድርገኸው እንድታልፍ ያስችልሃል::

*"አንድን ነገር እንድትጀምር የሚያደርግህ የስሜት መነሳሳት ነው:: በነገሩ እንድትቀጥልበት የሚያደርግህ ግን ልማድ ነው" - Jim Rohn*

የአንድ ቀን ሽያጭ እንዴት የአንድን ንግድ ስኬታማነት ሊያመላክት ይችላል? ልማድ የስኬታማ ሰዎች መለዮ ነው:: የስሜት ግለትና መነሳሳት ምንጩ ውጫዊ ነው:: ይህ ደግሞ መልካም የሆነ ነገር ነው ምክንያቱም ወደ አላማችን እንድንዘልቅ የሚያነሳሱንን ወጪአዊ ሁኔታዎች ስለምንፈልግ ነው:: ይህ ውጫዊ ግፊትና ማነሳሳት ግን ከውስጥ በሆነ ልማድ ካልታገዘ የትም አይደርስም:: በሌላ አባባል ሻማን የሚያበራው ከውጪ የተለኮሰው የእሳት ተጽእኖ ነው:: ሻማን ግን በማብራት እንዲቀጥል የሚደርገው

የሻማው እሳትን የማቆየት የውስጥ ብቃቱ ነው፡፡ የስሜት መነሳሳትና የዲሲፕሊን ጉዳይም እንዲሁ ነው፡፡ የውጪ ግፊት ያስጀምርሃል፤ የውስጥ ዲሲፕሊን እንድትዘልቅ ያደርግሃል፡፡ እውነተኛ የውስጥ ዲሲፕሊን ከሌለህ ግን አንተን ስኬታማ እንድትሆን ሊያግዝህ የሚችል ኃይል በዚህ ምድር ላይ ተፈልጎ አይገኝም፡፡

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው የመዘጋጀት እንቅፋቶች፡-

1. ስንፍና
2. ግድ የለሽነት
3. የልማድ ጉድለት

*ሕይወት ግሩም የሆኑ እድሎችን የምትሰጠው ለተዘጋጁት ነው፡፡*





# 21

## "ቢዚ ነኝ ተውኝ!"

### የጊዜ አጠቃቀም ቁልፍ



ቀናችንን የምናሳልፈው በምን ላይ ነው? በአስፈላጊው ወይስ በአጣዳፊው? ቀኑ አልቆ ማታ ወደ ቤታችን ስንገባ፣ መለስ ብለን ውሎአችንን ስናስበው ብዙውን ጊዜአችንን የወሰደው ነገር ምን ያህል ቁም ነገር ያለው ጉዳይ ነው? ከአስፈላጊው ጉዳይ ላይ ትኩረታችንን የወሰደው አጣዳፊውና አንገብጋቢው ነገር ምንድን ነው? የተግባር "ቅጠራ" እና "ቁጥጥር" ካላደረግን ያልታሰበና የቀስ በቀስ ሞት መሞታችን አይቀርም - ለሕይወትና ለእድገት የሚሆኑትን ትተን ለጊዜአዊ ስሜት ግለት በሆነው እንወሰዳለንና፡፡ ብዙ ሰዎች "ቢዚ" ናቸው - እስከሞት ድረስ "ቢዚ"!

በአለም በትልቅነቱና በዝናው ተወዳዳሪ ያልተገኘለት መርከብ - ታይታኒክ! ይህ መርከብ እጅግ ትልቅና በፍጹም ምንም ነገር ሊያሰጥመው አይችልም የተባለለት መርከብ ነበር፡፡ ቅጽል ስሙ፣ "የማይሰጥመው መርከብ" ነው፡፡ እንደውም ይህንን መርከብ የሰሩት ሰዎች "እግዚአብሔር እንኳ ሊያሰጥመው አይችልም" በማለት አጋንነው በድፍረት ይናገሩለት ነበር፡፡ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1912 ዓ/ም አንድ ነገር ተከሰተ፡፡ መርከቡ በጉዞ ላይ እንዳለ፣ በፊቱ የበረዶ ክምር እንዳለ ማስጠንቀቂያ ለካፒቴኑ ይደርሰዋል፡፡ ካፒቴኑ ማስጠንቀቂያውን ከቁጥርም አልከተተው፡፡ በባህር ላይ የሚገኙ የበረዶ ክምሮች

(Iceberg) ጫፋቸው ትንሽ፣ ከታች በውኃው የተሸፈነው አካላቸው ግን ግዙፍ በመሆናቸው ይታወቃሉ:: ይህ ካፒቴን ለስድስተኛ ጊዜ ማስጠንቀቂያው ሲመጣለት የሰጣቸው ምላሽ፣ "ቢዚ ነኝ ተውኝ" የሚል ነበር:: ይህ ቃል የካፒቴኑ የመጨረሻው ቃል እንደ ነበረ ይነገራል:: ብዙም ሳይቆይ ታይታኒክ በደረሰበት የግጭት አደጋ ለመስጠም በቃ:: የብዙ ሰዎች ሕይወት አለፈ፣ ብዙ ከስረትና ሃፍረት ደረሰ - በአንድ ሰው እስከሞት በሆነ ቢዚነት!!!

*"ምንም ከማያከናውን ቢዚነት ምንም አለማድረግ ይሻላል" – Unknown Source*

እስቲ የከተማችንን ሩጫ አስበው፣ ሕዝቡ (እኔና አንተን ጨምሮ) ይሮጣል! የስልካችንን ጥሪ ብዛት ደግሞ አስተውለው፣ የትኛው ጥሪ ትርጉም አለው? የጓደኝነትህን መረብ ሰፊነት አጢነው ስንቱ ጥልቅና ውጤታማ ነው? አብዛኛው ሰው ብዙ ስራ የለውም፣ ነገር ግን ሃያ አራት ሰዓት በፍጹም አይበቃውም:: በአንድ ጊዜ ከብዙ ሰዎች ጋር በተለያዩ ስፍራዎች ቀጠሮን ደራርበን እንይዛለን:: ስለዚህ ከአንዱ ጋር ካፌ ቁጭ ብለን እያወራን ሌላኛው በስልክ ያገኘናል::

መልሳችን፣ "እየመጣሁ ነው፣ ደርሻለሁ" የሚል፣ ዘጠና በመቶ ውሸት፣ አምስት በመቶ እውነት፣ አምስት በመቶ ደግሞ ግራ መጋባት የሞላው መልስ ነው:: የምናደርገውን አናውቀውም:: የት መሆን እንደፈለግን እርግጠኞች አይደለንም - "ቢዚነት"! ምንም ከማያከናውነው አይነት "ቢዚነት" እንዴት መዳን ይቻላል? የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ::

## ቢዚነት ወይስ ውጤታማነት?

ቢዚ መሆን ማለት ውጤታማ መሆን ማለት እንዳልሆነ በሚገባ አስታውስ:: ቀደም ሲል ለመመልከት እንደሞከርነው፣ በእጅህ ላይ አንድ መቶ ብሎኬቶች ቢኖሩህ መቶ የተለያዩ ሰፈሮች በመዘዋወር አስቀምጠሃቸው ብትመጣ፣ አንተ እጅግ በጣም ቢዚ ሰው





ነህ - የገነባኸው ነገር ግን የለህም:: እነዚህን ብሎኬቶች በአላማና በእቅድ አንድን ግንባታ ለመስራት ብትጠቀምባቸው ግን ቢዚም ነህ ውጤታማም ነህ:: ስንት ጓደኛ አለህ? በቀን ውስጥ ስንት ቀጠሮ ትይዛለህ? ብዙ ጊዜህን የምታጠፋው ምን ላይ ነው? ለረጅም ጊዜ ያደረከውን አንድ ነገር አስብና ውጤቱን አሰላስል፣ ያንን ነገር ያን ያህል ረጅም ለሆነ ጊዜ አድርገኸው ምን ፍሬን አይተሃል? እባክህን፣ የሩጫ ብዛትንና ውጤታማነትን አታምታታ::

*"ምን ያህል ቢዚ ሆነህ ብዙ እንደሰራህ አትንገረኝ፣ ምን ያህል ውጤት እንዳገኘህ ንገረኝ"*
*- James Ling*

የሕይወት ጥራት በውጤት እንጂ በሩጫ ብዛት አይለካም:: ግንባታው አካባቢ የሚራሯጠው ሰው ብዛት፣ የንትርኩ ግለትና የሚንኳኳው ድምጽ መጉላት ከስኬታማነትና ከውጤታማ ግንባታ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: ስኬት የሚለካው የምናደርገውን ነገር በማወቅና የሚገባንን ነገር በተገቢው ሰአት በማከናወናችን ነው:: አንዳንድ ሰዎች ከአንዱ ቀጠሮ ወሌላው ሲሮጡ፣ ከአንዱ ተግባር ወደ ሌላኛው ሲወራጩና በሰዓት ጭንቅንቅ ምክንያት ወደዘገዩበት ቀጠሮ አለክልከው ሲደርሱ ነው ሕይወትን የኖሯት የሚመስላቸው::

ከአንዱ ወደሌላኛው ተግባር የመሯሯጥ ልማድ በስኬታማነታቸው ላይም ሆነ በጤንነታቸው ላይ ያለው ጠንቅ ብዙም አይታያቸውም:: አንባቢዬ ሆይ፣ ሩጫህን አትቁጠር፣ ውጤትህን ቁጠር!

## ልፋት ወይስ ብልሃት?

ማንኛውም ውጤት ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በዚያ በተሰማራበት መስክ ብዙ መስራት እንዳለበት እሙን ነው:: ተግቶ የመስራት እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያንን

የምንተጋለትን ነገር ከዚህ በተሻለ ብልሃት ብሰራው ምን ያህል ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ አተርፋለሁ ብሎ መጠየቁም ያንኑ ያህል አስፈላጊ ነው:: ብዙ ሰዓት አቃጥለህና ብዙ ላብ አፍስሰህ የምታገኘውን ውጤት በጥቂት ጊዜና ካለምንም ልፋት ማጠናቀቅ ከቻልክ ለምን ከባዱን መንገድ ትመርጣለህ? አንዳንድ ሰዎች ሕይወትን የኖረት ቁና ቁና ስለተነፈሱ ይመስላቸዋል:: ስራዎችህን በልፋት ከመስራት በጥበብ ወደመስራት የምትለውጥበትን መንገድ መፈለግ ስኬታማ ያደርግሃል:: ማንኛውም አይነት ስራ በመጠኑም ቢሆን ልፋትንና ድካምን መጠየቁ እሙን ቢሆንም፣ የተሻለ መንገድ እያለ ከለመዱት መውጣትን አለመፈለግ ግን የስኬተ ቢሶች ድርሻ ነው::

*"ብቃት የተሞላው ስራ ማለት ጠንክሮ የመስራትና በብልሃት የመስራት ጥምረት ነው" - Byron Dorgan*

ይህንን እውነታ ለመገንዘብ በሃገራችን በልማድ የምንሰራባቸውን የአሰራር ሁኔታዎች መመልከት በቂ ነው:: ለምሳሌ፣ የግብርና ጥበብ ልቆ በሄደበት ዘመን በበሬ ማረስ ከአቅም ማጣት አንጻር ሲታይ ምንም አይደለም:: ለመሻሻል ክፍት ካለመሆን አንጻር ሲታይ ግን የሞኝነት ምልክት ይሆንበናል:: በሌላ አባባል፣ አሁን ከምትጠቀምበት ስልት የተሻለና የቀለለ ሌላ ስልት እያለ በእጅ ያለውን ስልት አለመልቀቅ ሞኝነት ነው:: የትኛው ይሻልሃል - በደነዘዘ መጥረቢያ ዛፉን ሲቀጠቅጡ መዋል ወይስ መጥረቢያውን ለመሳል ጥቂት ጊዜ ወስዶ በአጭር ጊዜና በአናሳ ጉልበት ዛፉን መቁረጥ:: ብዙ ሰዎች መጥረቢያውን ለመሳል ሰላሳ ደቂቃ ስለሌላቸው በአስራ አምስት ደቂቃ መቁረጥ የሚቻለውን ዛፍ ለመቁረጥ አምስት ሰዓት ይፈጅባቸዋል::

## አስፈላጊው ወይስ አጣዳፊው?

የአንተን ትኩረት የሚፈልገው ጉዳይ ብዙ ነው:: ብዙ እቃቸውን እንድትገዛቸው የሚፈልጉ ነጋዴዎች አሉ:: በርካታ ፍቅርህን የሚፈልጉ የፍቅር ጠያቂዎች ዙሪያህ ሊኖሩ





ይችላሉ:: አዳምጠኝ፣ ተመልከተኝ፣ አንብበኝ የሚለው የመገናኛ ብዙሃን አቅርቦት ከቁጥር በላይ ነው:: የሃሳብህን በር ላንኳኳው ሁሉ ከመክፈት ለመዳን ከፈለግህ በአጣዳፊውና በአስፈላጊው መካከል መለየት የግድ ነው:: ጊዜህን በሚገባ ለመጠቀም ከፈለግህ ጥያቄ ያቀረበውን ተግባር ሁሉ ከማስተናገድ መቆጠብ አለብህ:: በምትኩ በአስፈላጊውና በአጣዳፊው መካከል መለየት ይገባሃል:: ብዙውን ጊዜ ሰዓትህንና ጉልበትህን የሚወስደው ራሱን እንገብጋቢና አጣዳፊ አድርጎ ያቀረበው ጉዳይ ነው:: ትኩረትህን ግን አጣዳፊ ከሚመስለው ነገር ላይ በማንሳት አስፈላጊ በሆነው ጉዳይ ላይ ማሳረፍ አለብህ::

*"ለአጣዳፊው ነገር ሳይሆን ለአስፈላጊው ነገር ታዛዥ ሁን" – Steve Dougherty*

ሃሳብህን ከሚነዘንዝህ ነገር ላይ በማንሳት ወደ አስፈላጊው ለማዞር፣ ካለምንም ቅሬታና ትህትና በተሞላበት ዝንባሌ "እምቢ" የማለትን ልማድ ማዳበር አለብህ:: መልእክትህ "እምቢ" ቢሆንም እንኳ፣ አማራጭ አባባሎች ማዳበር ጥበበኛ ያደርግሃል:: ለምሳሌ፣ "ይህንን ነገር ባደርግልህ ደስ ይለኝ ነበር፣ ካለብኝ ሁኔታ የተነሳ ግን ማድረግ ስለማልችል ይቅርታ እጠይቃለሁ" አንዱ የትሁት አባባል ነው:: እንደዚህ አይነት የኑሮ ዘይቤዎች ለማዳበር ደግሞ የመገደድን ስሜት የማሸነፍ ጽንአት አስፈላጊ ነው::

የጠራውን ስልክ ሁሉ የማንሳት ግዴታ የለብህም:: ላገኘህ ያለህን ሰው ሁሉ የግድ ማግኘት የለብህም:: በማህበራዊ ኑሮ በተሳሰረና "ተባለ ... አሉ ... እየተባለ ይወራል ... " የሚሉትን ሃሳቦች ሰው ሁሉ በሚፈራበት አካባቢ መኖርህ እሙን ነው:: ይህ ሁኔታ ደግሞ በአስተሳሰብህ ላይ ታላቅ ጫና ማምጣቱ አይቀርም:: ለሕብረተሰቡ ተስማሚ ሆኖ ማደርና ባህሉን ማክበር መልካም ሆኖ ሳለ የአንተ ሕይወት ግን የአንተ እንደሆነ አትዘንጋ:: የዛሬ ጤና ቢስ ውሳኔህን መራራ ፍሬ መብያ ሰአት ሲመጣ፣ ይሉኝታቸውን የፈራኸው ሰዎች ያንን መራራ ፍሬ በፍጹም አይጋሩህም::



Scanned with CamScanner

የለብህም:: ምናልባት፣ "ስኬታማ ሰዎች ራሳቸውን የመቀበል ችግር የማይኖርባቸውም፣ ስኬታማ ሰዎች ስለሆኑ ነው"፣ ብለህ ታስብ ይሆናል:: ልታስብ የሚገባው ግን በተቃራኒው ነው:: ስኬታማ ሰዎች ወደዚያ ስኬት ከመዝለቃቸው በፊት ራሳቸውን የተቀበሉ ሰዎች ናቸው:: ራሳቸውን የመቀበላቸው ሁኔታ ነው ለስኬት ምቹ ያደረጋቸው:: በአንተም ሕይወት እንዲሁ ነው:: ምንም ውጤት ከመጠበቅህ በፊት ራስህን መቀበል የግድ ነው:: አለዚያ የምታገኛቸውን መልካም ነገሮች በሙሉ ራስህን ለማግኘት ስትል ትከፍላቸዋለህ፣ ከእጅህም ታጣቸዋለህ:: ተቀባይነት ፍለጋ በእጃቸው የገባውን ሁሉ ያጡ ሰዎች ቁጥራቸው ጥቂት እንዳልሆነ አትዘንጋ::

## ጠላትህን ጣለው

የውጭ ጠላት የለህም፤ የውስጥ እንጂ:: የአንተ ቀንደኛ ጠላቶች በማንነትህ ላይ የጨማመርካቸው አጉል ልማዶችህ ናቸው:: ይህ የውስጥ ጠላት ቀስ በቀስ ወደማንነትህ ሰርጎ የገባው ስሜታዊነትህ፣ አጉል ልማድህና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: እነዚህን አጓጉል ባህርያት ተመልከታቸው፣ በእነዚህ ነገሮች ውስጥ ሆነህ አልተወለድክም:: በሕይወት ጉዞህ የለቀምካቸው ጉዳዮች ስለሆኑ ልትጥላቸውና ልትለውጣቸው ትችላለህ:: እንግዲህ ቀደም ብለን የጠቀስነውን በፍጹም ልትለውጠው የማትችለውን ማንነትህን ከመቀበል ውጪ ምንም ምርጫ የለህም:: በዚህ ማንነትህ ላይ ጥላ ያጠላውን የባህሪና የአጉል ልማድ ችግር ግን መቅረፍ የግድ ነው:: ሁኔታህ ሲከብድ የምትሸነፈው ከእነዚህ የውስጥ ጠላቶችህ የተነሳ እንጂ ከምንም አይደለም::

*"ከፉ ልማዶች እንደምቹ አልጋዎች ናቸው፣ ለመግባት ቀላል፣ ለመውጣት ግን ከባድ" - Unknown Source*

ጤና ቢስ ልማዶችን ለመጀመር እጅግ ቀላል ነው፤ እነዚህን ልማዶች ግን ለማቆም ከባድ ነው::





ከሁሉ የሚመረጠው ቀድሞውኑ አጓጉል ልማዶች እንዳይነግሱብህ መጠንቀቁ ነው:: ራስህን በማይሆን ልማድ ውስጥ ካገኘኸው ግን ያንን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው:: ከፉ ልማድ እንደ እንግዳ ቀስ ብሎ ይገባል፣ ከጊዜ በኋላ ግን እንደ ጌታ ይገዛሃል:: ማንኛውንም ራስህን ሆነህ እንዳትኖር የሚያደርጉህን ባህሪያትና አመለካከቶች ለመተው የእነሱን ተቃራኒ ልማድ መጀመር የስኬት መንገድ ነው::

## ራስህን አሳድግ

በዚህ አለም ላይ ለመሸነፍ ታልፈህ የምትሰጠው ራስህን ባለህበት ለመቆም አሳልፈህ ስትሰጥ ብቻ ነው:: በፊትህ የሚደነቀርን ማንኛውም እንቅፋት የምታልፈው ራስህን ወደሌላ ማንነት በመቀየር ሳይሆን ራስህን በማሳደግ እንደሆነ አትዘንጋ:: ለምሳሌ፣ የብቸኝነትን ችግር ለማሸነፍ ሰዎች ቡድናቸው ውስጥ እንዲቀበሉህ እነሱን ወደመምሰል ራስህን መለወጥ የለብህም:: አለዚያ፣ ማንነትህን ለመለወጥ ሞከረህና ያልሆንከውን መስለህ ታይተህምንም እንኳ አዲስ ቡድን ብታገኝ፣ ከራስህ ጋር ስለተለያየህ ብቸኝነቱ ብሶ ታገኘዋለህ:: በሌላ አባባል ራስህን በመለወጥ ከችግርህ ሸሽተህ ማምለጥ አትችልም:: ማንነትህን ከችግሩ በላይ በማሳደግ ግን ዘላቂ መፍትሄ ታገኛለህ::

*"አንድ ሰው ለሰው ዘር ሊያበረክተው የሚችለው ትልቁ ስጦታ ራሱን የማሻሻል ስጦታ ነው" - Frank Herbert*

ራስን ማሳደግ የሚጠቅመው ለአንተ ብቻ አይደለም፣ ለሕብረተሰቡም ጭምር እንጂ:: ያደገ ማንነት፣ ያደገ አመለካከትና የበሰለ እይታ ያለው ሰው ለሕብረተሰቡ ታላቅ ስጦታ ነው:: ራሱን ማሳደግ ልማዱ ያደረገ ሰው ምንም አይነት ችግር ቢመጣ ለመጋፈጥ የተዘጋጀ ሰው ነው:: ምክንያቱም ይህ ሰው የሚመለከተው የችግሩን ግዝፈት ሳይሆን ከችግሩ በላይ የመሆንን ብቃት ሊያዳብር እንደሚችል ነው:: ራሱን የማያሳድግ ሰው



Scanned with CamScanner

የቤተሰብ፣ የሕብረተሰብና የሃገር ሸክም ነው:: ዘወትር የሚደረግለትንና ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም እንጂ እርሱ ሊያደርግ የሚችለውን ነገር አያስብም::

ካልተደረገለት ስላልተደረገለት ይነጫነጫል፣ ሲደረግለት ደግሞ በቂ እንዳልተደረገለት ያኮርፋል:: እንዲህ አይነት ሰው ጥፋት አጥፍቶ እንኳ ሃላፊነቱን በሰው ላይ ይጥላል:: በአንጻሩ ዘወትር ራሱን የሚያሻሽል ሰው ለማደግ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከመብዛቱ የተነሳ ለተራ ነገር ጊዜም አይኖረው::

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው ራስን የመሆን ቁልፎች:-

1. ወዳጅህን ተቀበለው
2. ጠላትህን ጣለው
3. ራስህን አሳድግ

> አንዳንዶች ከሰዎች ጋር መስሎ በማደር፣ ያላመኑበትን ነገር በማድረግ፣ ውስጣቸው ከሚያስበው ተቃራኒ በመናገር ራሳቸውን ቀይረውና ከማንነታቸው ወጥተው ይኖራሉ::





# 23

# አእምሮዬን ስምን አጨናንቀዋለሁ?

## የተግባራዊ እውቀት ቁልፍ



አእምሮህን የሞላው መረጃ ነው ወይስ ተግባራዊ እውቀት? የምታውቀው እውቀት ምን ያህል ተግባራዊ ነው? ብዙውን ጊዜህን በማጥፋት የምታጠናቸው የእውቀት አይነቶች ምንድን ናቸው? አንዳንድ ሰዎች ያላቸው የእውቀት ብዛት አስገራሚ ነው፣ የእውቀቱ አይነት ግን መረጃ ከማቀበል ወይም የአጠቃላይ እውቀት ውድድርን ከማሸነፍ ውጪ ለምንም ጥቅም አይውልም:: ማን የምን ቡድን ተጫዋች እንደሆነ፣ የትኛው ተጫዋች ስንት ብር እንደሚከፈለው፣ የከተማው ሃብታም ስም ከነአባቱና ከነአያቱ፣ ... መረጃው ብዙ ነው - ማንንም የማይረዳ መረጃ!!! እውነተኛ ስኬት ውስጥ ለመድረስ ከመረጃ ቋትነት ወጥተህ ወደተግባራዊ የእውቀት አዋቂነት ለመሻገር መወሰን የግድ ነው::

*"መረጃ ማለት እውቀት ማለት አይደለም" – Albert Einstein*

የታወቀው ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን አንድ ጊዜ ሰዎች በተለያዩ ጥቃቅን ጥያቄዎች እንዳደከሙት ይነገራል:: ከጥያቄዎቹ አንዱ፣ "አንድ ማይል ስንት ጫማ ነው" (በአገራችን አቆጣጠር አንድ ኪሎ ሜትር ስንት ሜትር ነው እንደ ማለት ነው) የሚል ነበር:: የአልበርት መልስ እንዲህ የሚል ነበር፣ "በአንዲት ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ በቀላሉ

የማገኘውን ቀላል መረጃ ቢቃሊ ለመያዝ በመሞከር አእምሮዬን ለምን አጨናንቀዋለሁ?":: ሄንሪ ፎርድ የተሰኘው የፎርድ መኪናዎች ድርጅት ባለቤትና ባለሃብትም በተመሳሳይ ሁኔታ ጋዜጠኞች በጥያቄ ሲያደከሙት የመለሰው መልስ ተመሳሳይ ነበር:: ጠያቂዎቹ የተለያዩ ታዋቂ ሰዎችን ስም እየጠቀሱ "እከሌን ታውቀዋለህ? ... እከሌስ ማን ነው? ... ይህና ያኛው ጦርነት የተካሄደው በስንት አመተ ምህረት ነው? ... " በማለት አደከሙት:: መልሱ አጭር የሚል ነበር፣ "የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ በቃሌ አላውቅም:: ነገር ግን መልሱን የሚነግራችሁ ሰው በአንድ ጊዜ ልጠቁማችሁ እችላለሁ"::

የአንዳንድ ሰዎችን አእምሮ የሞላው መረጃና እውቀት ከጊዜአዊ ደስታና በማኪያቶ ጊዜ በሚደረግ ክርክር በልጦ ከመገኘት አያልፍም:: በሃገሩ ውስጥ ያለ ሃብታም ስም ከነአያት፣ ባለሃብቱ ስንት ብር ባንክ ውስጥ እንዳለው፣ በዚህ አመት ስንት እንዳተረፈ፣ ስንቴና መቼ እንደተዘረፈ፣ ስንቴ አግብቶ እንደፈታ ... ይተረትሩታል:: በከተማው ውስጥ የሚነዳው የመኪናውን አይነትና ዋጋ ... የሰፈሩ ሰው ሁሉ የፍቅር ሕይወት ታሪክ ... የእንግሊዝ ቡድን ተጫዋቾችን ስም ከነሕይወት ታሪካቸው ... መረጃዊ-እውቀቱ ብዙ ነው፣ ተግባራዊነቱ ግን ጥቂት ነው::

እነዚህን ሁኔታዎች ማወቅ ክፋት ኖሮት ሳይሆን አንድ ሰው የግሉን ሕይወት የሚያሻሽልበትን እውቀት ለማግኘት ብቃቱም ሆነ ፍላጎቱ እንደሌለው እየተናገረ ይህን ያህል መረጃ በአእምሮው ለማከማቸት መቻሉ አንድ የተዛባ ነገር እንዳለ አመላካች ነው:: ከመረጃ ማሽንነት ውጣ፣ ወደ ተግባራዊ እድገት ዘልቀህ ግባ::

ተግባራዊ እውቀት ማለት ተጠቅመህበት አንድን ነገር የምታሻሽልበትና የገቢ ምንጭ ሊያመጣልህ የሚችል እውቀት ማለት ነው:: "አእምሮዬን የሞላው መረጃ ብቻ ነው ወይስ ተግባራዊ እውቀት?" የሚለውን ለማግኘት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ጠቃሚዎች ናቸው:-





## ራሴንና ቤተሰቤን አሻሽልበታለሁ?

በአእምሮህ ውስጥ የሞላውን ነገር መረጃም በለው እውቀት፣ ተግባራዊነቱ አንተንና ቤተሰብህን ካላችሁበት ሁኔታ ትንሽ እልፍ እንድትሉ ካላደረጋችሁ አእምሮህን በዚህ ነገር መሙላትህ ትርጉም የለውም:: የግልህን ሕይወት ስታጤነው "አሁን ካለሁበት ሁኔታ የተሻለ የለም" ብለህ ከደመደምክና መድረስ የምትችልበት ደረጃ እንደደረስክ ራስህን ካሳመንከው ተሳስተሃል:: እውነቱ ግን ይህ ነው:- ገና ሊታወቅ የሚገባው ብዙ ነገር አለ:: ራስህን ልታሻሽልበት የሚገባህ ነገር ብዙ ነው፣ ማሻሻልም ትችላለህ:: የአንተ አእምሮ በተግባራዊ እውቀት ሲሞላና ራስህን ስታሻሽል የቤተሰብህም ሁኔታ ከአንተ ጋር መሻሻሉ የማይቀር ጉዳይ ነው:: ይህ እንዲሆን ግን በተለያዩ ጥቃቅን "እውቀቶች" አእምሮአቸውን ሞልተው እዚህና እዚያ እየተዘዋወሩ ሰዎችን ከማስገረም የማያልፍን መረጃ ሲደረድሩ ከሚውሉት መንደር መውጣት አለብ::

*"ማወቅ በቂ አይደለም፣ እውቀቱ በተግባር ላይ መዋል አለበት:: ፈቃደኝነት በቂ አይደለም፣ ፈቃደኝነቱ ወደ ተግባር መመንዘር አለበት" - Johann Wolfgang Von Goethe*

ቀደም ብለን ለመመልከት እንደሞከርነው በመረጃና በእውቀት መካከል ያለውን መሰረታዊ ልዩነት ተግባራዊ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ ነው:: ለዚህ ነው አንድን ነገር ማወቅ ለብቻው የትም አያደርሰንም ብለን የምናምነው:: በመጀመሪያ፣ የማውቀው እውቀት ከመረጃነት ያለፈ መሆኑን ማረጋገጥ አለብኝ::

በመቀጠልም ይህንን እውቀት በተግባር ላይ በማዋል ሕይወቴንና ቤተሰቤን ለመለወጥ ማቀድ አለብኝ::



Scanned with CamScanner

በመጨረሻም ከአቅድና ከፈቃደኝነት በማለፍ ተግባር ውስጥ መግባት የግድ ነው:: ያልተገበርኩት እውቀት መጨረሻው ኪሳራ ነው፣ ምክንያቱም ያንን እውቀት ለማካበት ያሳለፍኩት ጊዜ በከንቱ ባክኗልና ነው::

## የተሰማራሁበትን የስራ መስክ አሻሽልበታለሁ?

አንዳንድ ሰዎች የሚሰሩበትን መስሪያ ቤት እንደመጠቀሚያ ብቻ ነው የሚያዩት - ደመዎዝ የማግኛያ መንገድ:: ስለዚህም፣ ጉልበታቸውንና ሰዓታቸውን የሚችሉትን ያህል በመቆጠብ ከዚያ መስሪያ ቤት ማግኘት የሚችሉትን ያህል አግኝተው ዘወር የማለት ዓላማ ነው ያላቸው:: ይህ አመለካከት የትክክለኛና የጨዋ ሰው አመለካት አይደለም:: የምንሰራበት ስፍራ የግላችን፣ የመንግስት፣ ወይም የግለሰብ መሆኑ ምንም ለውጥ የለውም:: ይህንን የተሰማራንበትን የስራ መስክ ለማሻሻል የሚጠቅምን እውቀት የማዳበርና የመጥቀምም ሃላፊነት አለብን::

*"ሌሎችን በመርዳት ራሳችንን እንረዳለን - ምክንያቱም ለሌሎች የምናደርገው መልካም ነገር ሁሉ ዞሮ ዞሮ ወደ እኛው ስለሚመለስ ነው" - Flora Edwards*

እንደ እውነቱ ከሆነ የስራ መስካችንን ለማሻሻል የምናደርገው ጥረት የሚያሻሽለው እኛንው ጭምር ነው:: ጉዳዩን በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል:: በመጀመሪያ መስሪያ ቤቴን ሳሻሽልና የመስሪያ ቤቴ ውጤታማነትና ገቢ ሲጨምር፣ የእኔም ገቢ ከዚያው ጋር አብሮ የማደጉ ሁኔታ የጎላ ይሆናል:: በሌላ ጎኑ ደግሞ ባለኝ ተግባራዊ እውቀት መስሪያ ቤቴን ሳሻሽል የእኔ መኖር እጅግ እየተፈለገ ይሄዳል:: ይህን የመፈለግ ሁኔታ መጠቀም ያለብኝ መስሪያ ቤቱን ለመቆጣጠርና "የሄድኩ ቀን ወየውላቸው" ለማለት ሳይሆን፣ ጠቅሜ እኔም ለመጠቀም ሊሆን ይገባዋል:: ያም ሆነ ይህ በምሰራበት የስታ ቦታ የምዘራው መልካም ዘር ሁሉ ወደ እኔ መመለሱ አይቀርም::



Dr. Eyob Mamo [25 የስኬት ቁልፎች | 25 KEYS TO SUCCESS]

## የአካባቢዬንና የሃገሬን ሁኔታ አሻሽልበታለሁ?

በጭንቅላትህ ውስጥ የተከማቸው እውቀት ከመረጃነት አልፎ ሰፈርህን፣ መንደርህን፣ ከተማህንና ሃገርህን ለማሻሻል ካልጠቀመ ዋጋ ቢስ ነው:: ምርጫው ሁለት ነው - ወይ የሕብረተሰቡ ሸክም ነህ ወይ ደግሞ ሕብረተሰቡን የምትሸከምና ወደተሻለ ነገር የምታሻግር ሰው ነህ:: ከሸክምነት ወደ ተሸካሚነት የምትሸጋገረው በተግባራዊነቱ ለማህበረሰቡ በሚጠቅም እውቀት ስትሞላና እውቀቱንም ስትጠቀምበት ነው:: ስለገቢህ አትጨነቅ፣ ለሕዝቡ መፍትሄን የሚያቀርብ እውቀትን ስለማጎልበትህ ተጨነቅ:: ሕብረተሰቡ ለምታቀርብለት መፍትሄ ደስ ብሎት ገንዘብ ይከፍልሃል:: ሁኔታው ልታመልጠው የማትችለውን የእውነታ ዑደት አቅፏል:: ስትሻሻል ሌላውን ታሻሽላለህ፤ ሌላውን ስታሻሽል ደግሞ ተፈላጊነትህ ይበዛና አንተን የበለጠ የሚያሻሽል ደጅ ይከፈትልሃል::

*"ስኬት ማለት ሃገርህ ለአንተ ከምታደርግልህ የበለጠ ለሃገርህ ማድረግ ነው!" – Henry Ford*

በቅርቡ የምትኖርበትን አካባቢ ሊያሻሽል ስለሚችል ሁኔታ አስበህ ታውቃለህ? ዝንባሌህ፣ "እውቀት ስላለኝ የተሻለ ነገር ይገባኛል" ከሆነ ተሳስተሃል:: በምትኩ፣ እውቀት ስላለኝ ከዚህ የተሻለ ለሃገሬ ማድረግ ይገባኛል የሚል ዝንባሌን ልታዳብር ይገባሃል:: እውቀትህ ተደብቋል ወይስ ወጥቶ በተግባር ላይ ነው? ምናልባት፣ "እውቀት ደግሞ ይደበቃል እንዴ?" ብለህ ትጠይቅ ይሆናል:: መልሱ፣ "አዎን" ነው - እውቀት ይደበቃል:: እውቀትን ምንም ሳትጠቀምበት በአእምሮህ ውስጥ መደበቅ ትችላለህ:: አንዳንድ ሰዎች እውቀትን እንደ መቆጣጠሪያ ኃይል ለመጠቀም ይደብቁታል:: የሚያውቀው በማያውቀው ላይ መሰልጠን እንደሚችል ማለት ነው:: ይህ አይነቱ እውቀትና ዝንባሌ የበላይነት ስሜት እንዲኖርህ ከማድረግ ያለፈ ውጤት አይኖረውም:: እውቀትህን ከተደበቀበት አውጣው፣ ለወገንህም አውለው::

በዚህ ምእራፉችን የተመለከትናቸው ተግባራዊ እውቀትን ለማዳበር የሚጠቅሙ ጥያቄዎች:-

1. ራሴንና ቤተሰቤን አሻሽልበታለሁ?
2. የተሰማራሁበትን የስራ መስክ አሻሽልበታለሁ?
3. የአካባቢዬንና የሃገሬን ሁኔታ አሻሽልበታለሁ?

ስለገቢህ አትጨነቅ፣ ለሕዝቡ መፍትሄን የሚያቀርብ እውቀትን ስለማነልበትህ ተጨነቅ:: ሕብረተሰቡ ለምታቀርብለት መፍትሄ ደስ ብሎት ገንዘብ ይከፍልሃል::





# 24

# የታሰረው እግሩ ሳይሆን ጭንቅላቱ ነው

## የአመለካከት ቁልፍ



የምንችለውንና የማንችለውን ነገር የሚወስንልን ማን ነው? ለምን ይህንን ብቻ በማድረግ ተገደብን? እነዚህን ጥያቄዎች ለራሳችን ጠይቀን እውነተኛውን መልስ ብናገኝ ያቃተን ነገር እስካሁን ድረስ ያልሞከርነው ነገር እንደሆነ እንደርስበታለን:: ሰውነታችን አእምሮአችን የነገረውን ለመታዘዝና ለመፈጸም የተዘጋጀ ፍጥረት ነው:: አእምሮዬ ትችላለህ ሲለው ሊሞክር፣ አትችልም ካለው ደግሞ ላይንቀሳቀስ ተገድቦ ይገኛል:: በዚህ እውነታ ውስጥ የኦሎምፒክ ውድድሮች ክብረ-ወሰን የመስበራቸውንም ምስጢር እናገኘዋለን:: የጨከነና ራሱን ያዘጋጀ ሰው ክብረ-ወሰንን እንደሰበረ ይኖራል - የራሱን ክብረ-ወሰን! ይህንን አትዘንጋ - የውስንነታችን የመኖሪያ ስፍራ አእምሮአችን ብቻ ነው!

አንድ ሰው የተለያዩ እንስሶች ለተመልካቾች ትእይንትን ወደሚያሳዩበት ስፍራ ገንዘቡን ከፍሎ ከገባ በኋላ ገና እንደተቀመጠ ያየው ነገር ግር አለው:: ተራራ የሚያክለውን ዝሆን አንድ አጭር ሰው በትንሽ ሰንሰለት እግሩን አስሮ ወዲህና ወዲያ ያደርገዋል:: "እንዴት አንዲት ቀጭን ገመድ ይህንን ግዙፍ እንስሳ ልታስረው ትችላለች?" አንድን ሰው ለመጠየቅ ወሰነ:: ትእይንቱ አልቆ ሰው ሁሉ ሲበታተን ይህንኑ ጥያቄ በውስጡ እያጉላላ ወደ አሰልጣኙ እንደምንም ብሎ ደረሰ:: በውስጡ የጠየቀውን ጥያቄ

ለሰውየው በአንደበቱ ጠየቀው፣ "እንዴት አንዲት ቀጭን ሰንሰለት ይህንን ግዙፍ እንስሳ ልታስረው ትችላለች?" መልሱ አጭርና ግልጽ ነበር፣ "ዝሆኑ ገና ሲወለድ ጀምሮ ነው ይህቺ ሰንሰለት በእግሩ ላይ የታሰረችው:: ገና በለጋነቱ ሲታገላት አላሸነፋትም:: የዝሆኑ ጥንካሬ ግን ይህችን ሰንሰለት መበጠስ ደረጃ ከደረሰ ቆይቷል:: ዝሆኑ በውስጡ፣ "ይህችን ገመድ በፍጹም አልበጥሳትም" ብሎ ስለሚያስብ እንደታሰረ ይኖራል:: የታሰረው እግሩ ሳይሆን ጭንቅላቱ ነው::

*"አይኖችህ አይተው የሚነግሩህን አትመን:: የሚነግሩህ ውስንነትን ነው:: መገንዘብ የምትችለውን ያህል ተገንዘብ፣ የምታውቀውንና የምትችለውን ለይተህ እወቅ፣ ወደከፍታ የምትወጣበትን መንገዱን ታየዋለህ" – Richard Batch*

አንድ ሰው ካለበት ወጥቶ መሆን የሚገባውን ለመሆን ከፈለገ የግድ እስከዛሬ ያመነውን ነገር ለጥያቄ ማቅረብ አለበት:: ካለማቋረጥ፣ "ለምን?" ብሎ ካልጠየቀ ባለበት ሁኔታና አመለካከት ታስሮና ሃውልት ሆኖ ይኖራል:: "ሁኔታዬ ለምን እንደዚህ ሆነ?" "ይህንን ነገር ለምን አልቻለውም?" "ይህንን ነገር ለምን አመንኩት?" የሚሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ አለበት::

ሰዎች የተለያዩ ገደቦችን በፊታችን ሊያስቀምጡብን ይችላሉ፣ ከማሰብና ከመጠየቅ ግን ሊከለክሉን አይችሉም:: መልስ የምታገኘው ስትጠይቅ ነው:: እውነታና ብልሃት ላይ የምትደርሰው ስታስብ ነው:: ዝም ብለህ ሁኔታህን በመቀበልና ከአመታት በፊት የተነገረህን ገደብ አምነህ መኖር ይበቃሃል:: የተሳሳትከውን፣ "ተሳስቼ ነበር" በማለት አዲስ ነገርን ለመሞከር ካልተነሳህ ሁኔታህ አይለወጥም:: ይህንን አስታውስ፣ እስካሁን ያልቻልከው ነገር ያልሞከርከው ነገር ነው:: የገደቡህን ነገሮች እወቃቸው፣ ነገር ግን በፍጹም አትቀበላቸው:: ያመንካቸውን መልእክቶች ደግሞ ለማጣራት ምንጩን ለይተህ ማወቅ አስፈላጊ ነው:: የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::





## ስራስህ የነገርከው

የስነ-ልቦና ጥናት አዋቂዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ አንድ ሰው በአማካኝ በቀን ውስጥ 50 ሺህ ጊዜ ለራሱ ያወራል፣ ቃል-አልባ ሃሳቦችን ለራሱ ያስተጋባል ወይም ከራሱ ጋር ይነጋገራል:: ከዚያም አልፎ ጥናቱ እንደሚለው፣ ከእነዚህ ለራሳችን ከምንነግራቸው 50 ሺህ መልእክቶች መካከል 80 በመቶው አሉታዊ ወይም ጨለምተኛነት የተሞላባቸው መሆናቸውን ነው:: እነዚህ አሉታዊ መልእክቶች በራሳችን ላይ ከባድ የሆነን ተጽእኖንና ጫናን ያደርጋሉ:: "አልቻልኩም ... አቃተኝ ... ምን አይነት ሰው ነኝ? ማንም ለእኔ ግድ የለውም ... " እና እነዚህን የመሳሰሉት በውስጣችን በማሰላሰል ለራሳችን የምንነግራቸው ንግግሮች ተጽእኖአቸው ይህ ነው አይባልም:: እነዚህ ቃላት ውስጥን በሚያበረቱና አዎንታዊነትን በተሞሉ መልእክቶች ብንለውጣቸው ለብርታት ይሆኑናል::

*"ለራስህ የምትነግረው ነገርና የምታሰላስለው ነገር ባለጠጋ ወይም ደኃ፣ የተወደደህ ወይም የተጠላህ፣ ደስተኛ ወይም ኃዘንተኛ፣ ሰዎችን የምትስብ ወይም የምታርቅ፣ ኃይለኛ ወይም ደካማ የማድረግ አቅም አለው" - Ralph Charell*

ከሌላ አካል ከምንሰማው ነገር የበለጠ ለራሳችን የምንነግረው ነገር ተጽእኖው እጅግ የላቀ ነው:: ሰው ራሱን "ሲዘጋው" ወይም "አላናግርህም" ሊለው አይችልም - ሁሌ ከራሱ ጋር ነው:: ሰው ሃሳብን ላለማሰብ የማይችል ፍጡር ነው:: ይህ እውነታ ደግሞ የተስፋ መቁረጥ ወይም የተስፋ ጭላንጭል ምንጭ ሊሆን የሚችል እውነታ ነው:: ተስፋ አስቆራጭ የሚሆንበት ምክንያት ለራሳችን የምንናገረውን መቆጣጠር ካቃተንና በጨለምተኝነት የተሞላን ሰዎች ከሆንን ነው::

የተስፋ ምንጭ የመሆኑ ምስጢር ያለው ግን ለራሳችን አዎንታዊ መልእክትን በመንገር ኃይልን ለመሞላት ያለንን እድል በመጠቀም ውስጥ ነው:: አካላችንና ማንነታችን አእምሮ ከተሰኘው የትእዛዝ ማስተላለፊያ ጣቢያ የሚተላለፍለትን መልእክት በተግባር

አሁንም ደግሜ ላስታውስህ፣ ወሳኙ ነገር ምን እንደሰማህ አይደለም፣ ለዚያ ለሰማኸው ነገር የሰጠኸው ምላሽ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ወደ እነሱ የሚመጣውን መልእክት ዝም ብለው የሚቀበሉ አይነት ሰዎች ናቸው:: በአመለካከታቸውና በስሜታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያመጣ እንደሆነ እያወቁ እንኳ ደግመው ደጋግመው ራሳቸውን ለዚያው ነገር ያጋልጣሉ:: ብልህ ሰው አንድን ጤና ቢስ ነገር የሚሰማውም ሆነ የሚያየው አንዴ ብቻ ነው፣ ከማንነቱና ከአላማው ጋር እንደማይመጥን ካጣራ በኋላ በፍጹም አይደግመውም::

እንደ እውነቱ ከሆነ የምታነብባቸው መጻሕፍትና የምታያቸው ፊልሞች የማንነትህ ነጸብራቆች ናቸው:: ወይ ያንን ነህ፣ ወይም ደግሞ ወደ መሆን ትመጣለህ:: ስለዚህ ወደ ማንነትህ የምታስገባቸውን መልእክቶች የምታጣራ ሰው ሁን!

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው አመለካከትን የሚቀርጹ ሁኔታዎች:-

1. ለራስህ የነገርከው
2. ሰዎች የነገሩህ
3. መገናኛ ብዙሃን የነገረህ

ሰዎች የተለያዩ ገደቦችን በፊታችን ሊያስቀምጡብን ይችላሉ፣ ከማሰብና ከመጠየቅ ግን ሊከለክሉን አይችሉም::





# 25

# በጽኑ ከፈለከው ታገኘዋለህ

## በጽኑ የመፈለግ ቁልፍ



ያንኑ ተግባራችንን እያደረግን የተለየ ውጤት መፈለግ ሞኝነት ነው:: የተለየ ውጤት ከተፈለገ የተለየ ተግባርና ጥረት ውስጥ መግባት የግድ ነው:: ርካሽ ኢንቨስትመንት፣ ርካሽ ውጤት፤ ትንሽ ጥረት፣ ትንሽ ውጤት፤ ጥቂት ስራ፣ ጥቂት ገቢ፤ የአጭር ጊዜ ትምህርት የአጭር ጊዜ ውጤት:: በብርቱ የፈለከውን ማግኘትህ አይቀርም:: በጽኑ የመፈለግ ዝንባሌ ከሌለህ ግን ያልለፋህበት መልካም ነገር ፊትህ ቀርቦ ቢመጣም እንኳ አትጨብጠውም፤ ቢያስጨብጡህም እንኳ አታቆየውም፣ ትለቅቀዋለህ::

አንድ ጎልማሳ ወደ ግሪኩ ጥበበኛና ፈላስፋ ወደ ሶቅራጥስ መጥቶ፣ "እውቀትን እፈልጋለሁ፣ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?" ብሎ እንደጠየቀው ይተረካል:: ሶቅራጥስ ይህንን ጎልማሳ በቅርብ ወደሚገኝ ወንዝ ወሰደውና አንገቱን ይዞ ውኃ ውስጥ ደፍቆ ካወጣው በኋላ፣ "ምንድን ነበር የምትፈልገው?" አለው:: ጎልማሳው፣ "እውቀት" ብሎ መለሰ:: ይህንኑ ነገር ሶስት ጊዜ ካደረገውና ያንኑ ጥያቄ ጠይቆ ተመሳሳይ መልስ ካገኘ በኋላ በመጨረሻ፣ እንደገና ወደ ውኃ ከጨመረው በኋላ አንገቱን ይዞ ብዙ አቆየው":: ጎልማሳው አየር ስላጠረው ፈንቅሎ በመውጣት በጣም መተንፈስ ጀመረ:: ሶቅራጥስ -

"ለምን ገፍተኸኝ ወጣህ?" ጎልማሳው - "አየር ፍለጋ":: ሶቅራጥስ - "እውቀትንም ይህንን ያህል በጽኑ ከፈለከው ታገኘዋለህ"::

*"ለወራትና ለአመታት አስብ አስብና ዘጠና ዘጠኝ ጊዜ እሳሳታለሁ:: በመቶኛው ጊዜ መልሱን አገኘዋለሁ" – Albert Einstein*

ማንበብና መጻፍ ቢማሩ ሊጠቅማቸው እንደሚችል ለብዙ ዘመን ሲነገራቸው የነበሩ አዛውንት በፍጹም ሊማሩና ሊያውቁ እንደማይችሉ ሲናገሩ ቆይተው አሁን ዘመኑ መጥቶ በእጃቸው የሞባይል ስልክ ሲገባ እንደልባቸው ሲጠቀሙበት ማየት ያስገርማል:: ምንም የሞባይል አጠቃቀም ስልጠና ሲወስዱ አልታዩም፣ ሞባይል መጠቀምን በብርቱ ስለፈለጉት ብቻ ቻሉበት - በመጠኑም ቢሆን:: ፍላጎት - ጽኑ ፍላጎት! እውነታው ሞባይል ከመጠቀም ያለፈ ነው:: ተግባራዊነቱ እውቀትን ከመፈለግ ያለፈ ነው:: በሕይወትህ ልታገኘው የፈለከውን ማንኛውም አይነት ስኬት በጽኑ ከፈለግከው ማግኘትህ አይቀርም:: ሰው ከጻፈው ልታነብበው፣ ሰው ከደበቀው ልታገኘው፣ ሰው ከጠመጠመው ልትፈታው እንደምትችል ሲገባህና ልቦናህን ስትከፍተው ፈጠነም ዘገየም ዓላማህ ላይ መድረስህ አይቀርም:: ይህንን እውነታ ከእውቀት አንጻር ስንመለከተው፣ የሚከተሉትን ሶስት የእውቀት አይነቶች ለማወቅ በጽኑ እንድትከታተለው አበረታታሃለሁ::

## "ለምን" የሚለውን እውቀት እወቅ

በዚህ አለም ላይ በፍጹም የማያድግ አእምሮ "ለምን?" የሚለውን ጥያቄ የማይጠይቅ አእምሮ ነው:: ያሳዩትን ነገር ዝም ብሎ በማድረግና የሚከፈለውን ደመዎዝ ተቀብሎ በሚሄድ የተወሰነ ማንነት:: ተመልሶ ያንኑ ባለፈው ወር ያገኘውን ደመዎዝ ፍለጋ፣ ያንኑ ባለፈው ወር ሲያደርግ የነበረውን ተግባር የሚያደርግ ማንነት:: መሻሻልን የማይፈልግ፣ እውቀትን የማይከታተል ... ባለበት ለመሰንበት የተደላደለ ማንነት::





ስኬታማ ሰው እንዲህ አይደለም:: ስኬታማ ሰው እውቀትን ካለማቋረጥ ይከታተላል፤ በተለይም "ለምን?" የሚለውን እውቀት እስኪያገኝ አያርፍም:: ይህ ሰው አንድ የገባው ነገር አለ - በአለም የተገኙና የአለምን ታሪክ የለወጡ ግኝቶች በሙሉ፣ "ለምን?" ብለው በጠየቁና እውቀትን በጽኑ በፈለጉ ሰዎች እንደተገኙ ያውቃሉ::

*"አንድ ነገር እንዴት እንደሚደረግ የሚያውቅ ሰው ሁል ጊዜ ስራን ያገኛል፤ ያ ነገር ለምን እንደሚደረግ የሚያውቀው ግን ሁል ጊዜ የእርሱ አለቃ ይሆናል" - Diane Ravitch*

በመስሪያ ቤትህ ሁኔታዎችን አጢነህ ታውቃለህ? በዚያ ቦታ የሚሰራውን ስራ "እንዴት" እንደሚሰራ የሚያውቀው ሰው ቅጥረኛ ሆኖ በመስራት ራሱን ይገድባል:: በተቃራኒው፣ ስራው የሚሰራው "ለምን" እንደሆነ የሚያውቀው ግን አለቃ ሆኖ ታየዋህ - ከዚያም የራሱን ስራ ወደ መጀመር ሲሸጋገር:: ለምሳሌ፣ የምትሰራበት ማሽን "እንዴት" እንደሚሰራ አውቀህ በመቀጠር ምርት ክፍል ውስጥ ለሃያ አመታት ልትሰራ ትችላለህ:: በተቃራኒው ግን፣ "መስሪያ ቤቱ ለምን አላማ ተቋቋመ? ይህ ምርት የሚመረተው ለምንድን ነው? ለምን ይህንን የስራ ሂደት መረጥን?" ወደሚሉት የእውቀት አይነቶች ራስህን ብታሳድግ ወደ አለቅነትና ደመወዝህን ወደማሻሻል ከማደግህም ባሻገር ለሰው ከመስራት ለራስህ ወደመስራት እንደምትችል ጭላንጭሉን ታገኘዋለህ::ለሰው መስራት መጥፎ ሆኖ ሳይሆን፣ የራስህን ነገር ጀምረህ መስራቱ የበለጠ የጊዜና የገንዘብ ነጻነት ስለሚሰጥህ ነው:: በሁኔታውም አንተ፣ ቤተሰብህና የአገር ኢኮኖሚ ያድጋል::

## ተግባራዊውን እውቀት እወቅ

ቀደም ብዬ በሌላ ምእራፍ ለመግለጽ እንደሞከርኩት፣ ብዙ ሰዎች የሚያውቁት እውቀት ተግባራዊነት ስለሌለው የብዙ ለምንም ተግባራዊነት የማይውሉ እውቀቶች ማጠራቀሚያ ናቸው:: ለምሳሌ፣ በአለም ላይ ያሉትን የእግር ኳስ ቡድኖች ከነተጫዋቾቻቸው፣ ከነደሞዛቸውና ማን መቼ ዋንጫ እንደበላ ማወቅህ መልካም ነው::



Scanned with CamScanner

ይህ እውቀት ግን ከመዝናናት፣ የእለቱን የማኪያቶ ጊዜ ወሬ ከማጧጧፍና ውርርድን ከማሸነፍ ያለፈ ነገር ላይኖረው ይችላል:: በምትኩ፣ ዝንባሌዬ ከስፖርት እንዲወጣ አልፈልግም ካልክ፣ የኮችነት፣ የአሰልጣኝነት ወይም የዳኝነት እውቀት በሚገባ ብታውቅ ከመረጃ ያለፈና የገቢ ምንጭ የሚሆን እውቀት ይሆንልሃል:: አንዱ የጠቅላላና የመረጃ እውቀት ነው፣ ሌላኛው ግን ተግባራዊና ሕይወትህን ወደፊት የሚያራምድ እውቀት::

*"እውቀትንና ጥበብን አታምታታቸው - እውቀት በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልግህን ስራ ይሰጥሃል፣ ጥበብ ግን ጣእም ያለውን ሕይወት ይሰጥሃል" - Sandra Carey*

ጥበብ ማለት የምናውቀውን እውቀት ተግባራዊ የምናደርግበት ስልት ማለት ነው:: በዚህች አለም ላይ ቁጥራቸው ከመጠን ያለፈ ሰዎች ብዙ እውቀት ውስጣቸው አከብተዋል፣ ነገር ግን በፍጹም አይጠቀሙበትም:: አንድን ነገር ማወቅና ያንን እውቀት ተግባራዊ ማድረግ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: እውቀት ብቻውን ስኬታማ አያደርግም፣ እውቀትን በጥበብ ተግባራዊ ስናደርገው ብቻ ወደ ስኬት ዘልቀን እንሄዳለን:: መቶ ጥልቅ እውቀቶችን ከሚያውቅና አንዱንም ከማይተገብረው ሰው፣ አንዲት እውቀት አውቆ ያችንው የሚያውቃትን በተግባር የሚያውል ሰው እጅግ የላቀ ስኬታማነት ውስጥ ይገባል:: ለዚህ ነው ከእውቀትህ የተነሳ ትኖራህ፣ እውቀትህን በጥበብ መጠቀም ስትጀምር ግን ሕይወትን ማጣጣም ትጀምራለህ የምንለው::

## "ዘመናዊ" እውቀትን እወቅ

እውቀትህ "ያረጀ" እውቀት መሆኑን በምን ታውቃለህ? እውቀትህ "እያረጀ" የመምጣቱ አንዱ ምልክት፣ አውቀዋለሁ የምትለውን ነገር "ማሽን" እየቀየረው የመምጣቱ ሁኔታ ነው:: ሌላው ምልክት፣ በተሰማራህበት መስክ የሚመጡትን አዳዲስ መረጃዎችና ግኝቶች በማንበብና ስልጠናዎችን በመውሰድ ካላሻሻልክ እውቀትህ "አረጀ" ይባላል:: ለምሳሌ፣ የዛሬ 20 ዓመት የምትጠቀምበትን የታይፕ ማሽን አሁንም የምትጠቀም





ከሆንክ፣ ኮምፒውተር በሚያውቅ ሰው መቀየርህ አይቀርም:: የመዝገብ አያያዝ ዘይቤህ በዚያ መስሪያ ቤት የዛሬ ሃያ አምስት አመት ስትቀጠር በነበረበት፣ ጠረጴዛ በሚያከል ደብተር ላይ ከቆመ፣ አንተን በዚያ ስራ ላይ እስካሁን ያቆየህ አገነውልህ ነው እንጂ ብዙም አያዛልቅህም:: አእምሮህን ከፈት፣ ለዛሬ ሊታወቅ የሚገባውን እውቀት እወቅ:: "ምን አዲስ ነገር አለ?" ብለህ ጠይቅ::

*"በውኃ ላይ በመውደቅ ልትሰጥም አትችልም፣ እዚያው በመቆየት ግን ትሰጥማለህ" - Edwin Louis Cole*

ያለህበት ሁኔታ ለከስረትና ለኋላ ቀርነት ሊያጋልጥህ አይችልም፣ በዚያ መቆየት ግን ብዙ ያወርድሃል:: የሚሰጥም ማን ነው? በውኃ ላይ ከወደቀ በኋላ እዚያው የሚቀረው ሰው አይደለምን? ውዳቂ ማን ነው? ከወደቀ በኋላ ሳይነሳ በዚያው የሚቀር አይደለምን? የማያውቅ ማን ነው? ካለበት የእውቀት ደረጃ ለመውጣት የማይንቀሳቀሰው አይደለምን? በአጭሩ፣ አሁን ያለህበት የእውቀት ደረጃ ስኬተ ቢስ አያደርግህም፣ ከዚሁ እውቀት ጋር ግን ከአመት ወደ አመት አብረህ በመኖር ምንም አይነት አዲስ እውቀትን ለማዳበር የማትንቀሳቀስ ሰው ከሆንክ ስኬተ ቢስ የሚያደርግህ ይህኛው ነው:: እውቀትን በብርቱ ከፈለከው ማግኘትህ አይቀርም - ማንኛውንም አይነት እውቀት!!!

በዚህ ምእራፋችን የተመለከትናቸው እውቀትን በጽኑ የመፈለግ ቁልፎች:-

1. "ለምን" የሚለውን እውቀት እወቅ
2. ተግባራዊውን እውቀት እወቅ
3. "ዘመናዊ" እውቀትን እወቅ

*ሰው ከጻፈው ልታነብበው፣ ሰው ከደበቀው ልታገኘው፣ ሰው ከጠማጠመው ልትፈታው እንደምትችል ... ሲገባህና ልቦናህን ስትከፍተው ፈጠንም ዘገየም ዓላማህ ላይ መድረስህ አይቀርም::*

# ማጠቃለያ

የስኬት ቀመር (formula) ይህ ነው ብሎ በአንድ መጽሐፍ ለማስፈር የሚችል ሰው አለ ብሎ ማመን አስቸጋሪ ነው:: ስኬት ዘርፈ-ብዙ የመሆኑ እውነታ ስኬት በሂደት የሚገኝ መሆኑን አመልካች ነው:: በሌላ አባባል፣ ስኬት የሚደረስበት ጥግ አይደለም፣ ስኬት የኑሮ ሂደትና የኑሮ ዘይቤ ነው:: ሆኖም የስኬት መንገድ እውንና ተጨባጭ ነው:: የስኬትን ቀመር በተወሰኑ ገጾች አስፍሮ ለመጨረስ ያስቸግራል ብለን የምናምነው አብዛኞዎቹ የስኬት መንገዶች ራስን ከመምራት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ነው:: አመራር ደግሞ ሁኔታዊ ነው:: እውነትና የመርህ አስፈላጊት ሁኔታዊ ሊሆኑ አይችሉም - የህይወት መርህና የእውነት እውነተኛነት ሊለወጡ አይችሉምና! እውነትን በምን መልኩ ተግባራዊ እንደምናደርገው ግን እንደ እለቱ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል::

በአጭሩ ሲቀመጥ፣ ስኬት ማለት ራስን መምራት ማለት ነው:: ራስን የመምራት ምስጢር እጅግ አስገራሚ ምስጢር ነው:: ቤተሰብ፣ ልጅ አድጎለት ራሱን ወደ መቻልና ለየእለቱ ጥቃቅን ሁኔታ ቁጥጥር ወደ ማይይፈልግበት ደረጃ ሲደርስለት ደስታው ብዙ ነው:: ቁጥጥር የማይፈልጉ ሰራተኞች የበዙበት መስሪያ ቤት ምን ሊመስል እንደሚችል ማሰብ አያስቸግርም:: ሁኔታውን በሃገር ደረጃ ስንመለከተው፣ ራሳቸውን ለመምራት የበቁ ዜጎች ሲበዙ ሃገር ጤና ትሆናለች፣ መንገዶቻችን ንጹህ ይሆናሉ፣ መካሰስ ይቀንሳል፣ ማረሚያ ቤቶቻችን ባዶ መሆን ይጀምራሉ:: በቀላል ትርጓሜ፣ ስልጣኔ ማለት ዜጎች ራሳቸውን ወደ መምራት ተሻገሩ ማለት ነው:: ራሱን የማይመራን ሰው መመሪያ ሊመራው አይችልም:: አንዳንድ ሰው መመሪያ እንኳ ተሰጥቶት እንደገና መመሪያውን መከተሉን የሚያረጋግጥ መሪ ይመደብለታል:: እንዲህ አይነቱን ሰው ከስኬት ጋር ለማስተዋወቅ እጅግ አስቸጋሪና አድካሚ ነው::

ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ በማንበብ ወደ ስኬት አንድ እርምጃ ለመራመድ እንደወሰኑ አምናለሁ:: ቀሪው ዘመንዎም የስኬት እንዲሆንልዎ ታላቅ ምኞቴ ነው!





# References


1. Branden, N. (1994). The Six Pillars of Self-Esteem. Hyperion Books, New York, NY.
2. Brown, L. (1997). It is not Over Until You win. Simon & Schuster, New York, NY
3. Canfield, J. (2005). The Success Principles. HarperCollins. New York, NY.
4. Canfield, J. and Hansen, M. (1994). Dare to Win. Berkley Books, New York, NY.
5. Canfield, J.; Hansen, M. and Hewitt, L (2000). The Power of Focus. Health communications Inc. Deerfield Beach, FL.
6. Maxwell, J. (1993). Developing the Leader Within You. Thomas Nelson Publishers. Nashville, TN.
7. Maxwell, J. (2008). Go for the Gold. Thomas Nelson, Inc. Nashville, TN.
8. Maxwell, J. (2008). Success 101. Thomas Nelson, Inc. Nashville, TN.
9. Maxwell, J. (2009). How Successful People Think. Center Street, Hachette Book Group. New York, NY.
10. McGrow, P. (1999). Life Strategies, Doing What Works, Doing What Matters. Hyperion Books. New York, NY.
11. Osteen, J. (2004). Your Best Life Now. Time Warner Book Group. New York, NY.
12. Ruettinger, R. and Celizic, M. (1995). Rudy's Rules for Success. Doddridge Press, Dallas, TX.




Scanned with CamScanner

13. Schwartz, D. (1965). The Magic of Thinking Big. Simon & Schuster, Inc. New York, NY.

14. Zufelt, J. (2002). The DNA of Success. Regan Books, New York, NY

Scanned with CamScanner

